# ምዕራፍ አንድ፡-የፈጠራ ጽሑፍ

## የፈጠራ ጽሑፍ ምንነት

የፈጠራ ጽሑፍ በሚለው ሀረግ ውስጥ ሁለት መሰረታዊ ነጥቦችን ማየት ተገቢ ነው፡፡ እነሱም ፈጠራ እና ጽሑፍ የሚሉት ናቸው፡፡

**ፈጠራ** ሥንል እንደዚህ ኮርስ ብያኔ ከጽሕፈት ጋር የተያያዘውንና በቋንቋ አማካይነት የሚቀርበውን ፈጠራ ማለት ሲሆን ፈጠራ የምናብ ሀይልን ተጠቅሞ፡-

- *አዲስ የሆነ ሃሳብ ማፍለቅን*
- *ወጥ ስራ(Origina) ማግኘትን*
- *ያልነበረውን ማሳየት*
- *ሕልውና እንዲያገኝ ማድረግ*
- *ኪነ ጥበባዊ ገለጻም ነው*
- *በእስብ መራቀቅና አዲስ ነገር ማግኘት ማለት ነው፡፡*

ጽሑፍ ስንል ደግሞ በአጭሩ፡-

- *በቋንቀዋ አማካይነት የሚቀርበውን*
- *የፈጠራዊነት ባህርይ ያለውን*
- *በጽሑፍ የቀረበ ሃሳብን ወ.ዘ.ተ ማለት ነው*

ጽሕፈትን በተመለከተ የተለያ ምሁራን የተለያዩ ሃሳቦችን ሰንዝረዋል፡- ለምሳሌ ያህል

- ታሪኳን(1985) እንደሚለው ጽሕፈት
    - *ድርሰት የማዘጋጀት ስራ ነው፤*
    - *በቋንቋ አማካይነት የሚከወን*
    - *ችሎታንና ተሰጥዖን የሚጠይቅ፤(ማንኛውም ሰው ደራሲ አይደለም)*
    - *በቃል ከመግባባት ልዩ የሆነ (ምክንያት፡- ቃላዊ ተግባቦት በተለያዩ አካላዊና ድምጻዊ ምልክቶች የማይታጀብ)*
    - *ኢ ቀጥተኛ የሆነ ተግባቦት ነው ይለዋል፡፡ ኢቀጥተኛ መባሉ ደራሲና ታዳሚ በአካል የማይገናኙበት አውድ በመሆኑ ነው፡፡*

ሀርመር(2001) ደግሞ ጽሑፍ፡-

- *በጽሑፍ አማካይነት፡- ሃሳብን ፣ ስሜትን፣ እምነትን፣ ርዕዮተ ዓለምን፣ አመለካከትን፣ ፍልስፍናን ወ.ዘ.ተ* ለሌሎች *የምናተላልፍበት መንገድ/ ስልት ነው፤* ይለዋል፡፡

ጆናህ(2006) ደግሞ ጽሑፍ፡-

- *ተከታታይነት ያለው ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም በርካታ የጽሕፈት ደረጃዎችን ማለትም ቢጋር መንደፍ፣ ረቂቆችን መጻፍና ዋናውን ስራ መስራትና መከለስ የሚጠይቅ ኢቀጥተኛና ውስብስብ ተግባር(ፍካሬን፣ ትንታኔን፣ ብያኔን ክልሰፋን ወ.ዘ.ተ የሚጠይቅ) ነው፡፡ በተጨማሪም ጽሕፈት አዲስ ጽንሰ ሃሳብ የሚፈልቅበት፣ የሚንጸባረቅበት፣*
- *በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ብቃትን የሚጠይቅ(የዋናውን ሃሳብ/ ገጠመኝ የማቅረብ ችሎታ፣ የአደረጃጀት፣ የቃላት ምርጫ፣ የሰዋሰው ሥርዓትን በአግባቡ የመጠቀም፣ የአጻጻፍ ስርዓትን የሚጠነቅቅ)*

- *የሃሳብ እርቅቅቆትን የሚጠይቅ*
- *ፈጠራዊነቱ እጅግ የረቀቀ ተግባር ነው፣ በማለት ይገልጻል፡፡*

ከዚህ በላይ ፈጠራ እና ጽሑፍ ለሚሉ ሃሳቦች ከተሰጡ ብያኔዎች በመነሳት “የፈጠራ ጽሑፍ” የምናብ ሀይልን ተጠቅሞ፡- አዲስ ሃሳብን ወጥ ስራ የማፍለቅ፣ ያልነበረውን የማሳየት፣ ሕልውናየ እንዲያገኝ ማድረግ፣ በቋንቋ አማካይነት የሚከወን፣ ችሎታንና ተሰጥዖን የሚጠይቅ፤ በጽሑፍ አማካይነት፡- ሃሳብን ፣ ስሜትን፣ እምነትን፣ ርዕዮተ ዓለምን፣ አመለካከትን፣ ፍልስፍናን የሚገለጽበት፣ ትንታኔን፣ ብያኔን፣ ክልሰፋን፣ የሚጠይቅ፣ ገጠመኝን ፈጠራዊ በሆነ መንገድ የማቅረብ ችሎታን የሚጠይቅ፣ የሃሳብ እርቅቅቆትን የሚጠይቅ እጅግ የረቀቀ ተግባር ነው ማለት ይቻላል፡፡

ነገር ግን በዚህ መጠሪያ የሚታወቁ ጽሑፎች በስነጽሑፋዊ ባህሪያቸውና ይዘታቸው እጅግ የተለያዩ ከመሆናቸው የተነሳ በበርካታ የዘርፉ ምሁራን ዘንድ የፈጠራ ጽሑፍን ለመበየን ከመሞከር ይልቅ የፈጠራ ጽሑፍ የሆኑ ስራዎችን መዘርዘር በጣም የተሻለ ነው የሚል አመለካከት አለ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የፈጠራ ጽሑፍን ለመበየን ወይም የፈጠራ ካልሆኑ ጽሑፎች ለመለየት መሞከር እጅግ ፈታኝ ስራ በመሆኑና ለአንዱ የፈጠራ ጽሑፍ የሆነው ለሌላው ላይሆን የሚችልበት አጋጣሚ በመብዛቱ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ሁለቱን ጎራዎች የሚለየው መስመር በግልጽ ተለይቶ አይታወቅም፡፡

ከላይ በተሰጠው ብያኔ ላይ ተመስርተን እንደ ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት የመሳሰሉትን ጽሑፎች ያለጥርጥር የፈጠራ ጽሑፎች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ያሉትን ጽሑፎች ለማዘጋጀት የምናባዊና ፈጠራዊ አስተሳሰብ መኖር ግድ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ደረቅ እውነታን ብቻ ይዞ የቀረበን ጽሑፍ ስናነብ የፈጠራ ጽሑፍ አለመሆኑን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እንደ ልቦለድ ያሉት ጽሑፎች ፈጠራዊ የተባሉት የሚያዝኑ፣ የሚያስደስቱ ወይም የሚያሳዝኑ፤ በአጠቃላይ በምናብ ዋና መሳሪያነት ስሜትን ሰርስሮ የመግባት ሀይል ያላቸው ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡ ስለሆነም ደረቅ እውነታን ይዘው የሚቀርቡ ጽሑፎች- ማንኛውም ተግባር የአእምሮን የፈጠራ አቅም የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን- በተወሰነ ደረጃ የፈጠራ ችሎታን የሚጠይቁ ቢሆኑም፣ ይህ ሁኔታ ግን ከፈጠራ ጸሑፎች ጎራ ለመመደብ አያበቃቸውም፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ የፈጠራ ጽሑፍን ለመበየን በሚደረገው ሙከራ ላይ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥሩት በሁለቱ ጽንፎች መካከል የሚገኙ ሌሎች ጽሑፎች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በምናብ እንድንጓዝ በሚያደርጉ ድንቅ አገላለጾች የተሞላ ጥናታዊ ጽሑፍ ብናነብ ጽሑፉ በጸሐፊው ፈጠራ እንደተቀባ ወይም እነደተነካካ በግልጽ ይሰማናል፡፡ እንዲህ አይነቶቹ ጽሑፎች እንደየሰው አመለካከት ከሁለቱ በአንዱ ጎራ ይመደባሉ፡፡ በአጠቃላይ ግን ማንኛውም ደረቅ መረጃን ከማስተላለፍ ይልቅ በምናባዊ ፈጠራ ላይ ተመስርቶ ሀሳብንና ስሜትን መግለጽን አላማው ያደረገ ጽሑፍ ሁሉ የፈጠራ ጽሑፍ ሊባል ይችላል ብሎ ጊዜያዊ መግባባትን የሚፈጥር ጥቅል ብያኔ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

የፈጠራ ናቸው ተብለው የተፈረጁትም ጽሑፎች ቢሆኑ በመካከላቸው የሚገኘው የባህሪ ልዩነት እጅግ የጎላ በመሆኑ የተነሳ በሚጠኑበት ወቅት ተከፋፍለው መታየታቸው ግድ ሆኗል፡፡ በዚህም መሰረት በመጪዎቹ ምዕራፎች በስፋት እንደምናየው፣ የፈጠራ ጽሑፎች ልቦለዳዊና ኢ-ልቦለዳዊ ተብለው በሁለት ታላላቅ ጎራዎች ተከፍለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ደረጃው ቢለያይም ሁሉም አይነት የፈጠራ ጽሑፎች ምናባዊና ፈጠራዊ መራቀቅን የሚጠይቁ በመሆናቸው የጥበብ ስራዎች መሆናቸው የሚያስማማ ጉዳይ ነው፡፡ እንደአሜሪካዊቷ ደራሲ ጆይስ ካሮል አዌትስ አባባል "ጥበብ ጥልቅ ከሆነው ግለሰባዊ ማንነት ይመነጫል፡፡" (2003፣35) ቅርጽ አሲዞ የሚያቀርበው ባለሙያ ደግሞ ጥበበኛ ነው፡፡ በመሆኑም የፈጠራ ጽሑፍ የደራሲውን ጥልቅና ገደብ የለሽ ምናባዊ ጉዞና ፈጠራዊ አስተሳሰብ የሚጠይቅ፣ ሀሳብና ስሜት ውብና ስሜት ነኪ በሆነ መልኩ የሚቀርብበት ጥበብ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ደረቅ መረጃን በተለመደው መንገድ የሚያስተላልፍ ጽሑፍ የፈጠራ ጽሑፍ አይደለም፡፡ የፈጠራ ጽሑፍ እውነታን በደረቁ ከማቅረብ በተቃራኒው መንገድ በመሄድ ስሜትንና ምናባዊ ምስሎችን መግለጽ ላይ ያተኩራል፡፡ ለምሳሌ ስለዛፍ አቆራረጥ አንድ ጋዜጠኛ እንዲዘግብ ቢጠየቅ ምናልባት ሊጽፍ የሚችለው ነገር "አንድ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው እንዲህ ባለው ስፍራ ከሚገኘው ጫካ ገብቶ አንድ ዛፍ በመጥረቢያ ቆረጠ፡፡ ዛፉ በወደቀበት ወቅት በአካባቢው የነበሩ ሌሎች እጽዋቶችን በመደምሰስ ጉዳት አድርሷል፡፡" የሚል ይሆናል፡፡ ይህን ሃሳብ ገጣሚ ሰይፉ መታፈሪያ "እርካታ" በተሰኘው ግጥሙ በሚከተለው መልኩ በግጥም ሲገልጸው እንመልከት፡፡

> እየቀጠነ ሄደ እየቀጠነ
> ጭብጥ እየመጠነ
> ውፍረቱ፣
> እየተቀረደደ ቅርፊቱ
> እየሰለለ ክርክራቱ
> ግንድ ንጣቱ፡፡
> ቀቅ! ቀቅ! ቀቅ!
> እና ው-! ድቅ!
> ዛፍ ግርስስ-ተገረሰሰ
> ሳር ቅጠሉን ደመሰሰ!
> እና ቆም ብሎ ያየው ጀመር
> ደገፍ ያለው ደገፍ
> ምሳሩን
> እየጠራረገ ግንባሩን፡፡

በዚህ ግጥም ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የአስተውሎት ወይም ምልከታ ሀይል እንዳለና ሀሳቡ የቀረበበትም መንገድ ስሜትን መሰረት አድርጎ ምስል የሚከስት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ብያኔና ምሳሌ በመነሳት በመነሳት የፈጠራ ጽሑፍ በስሜት ህዋሳት በኩል በሚሰበሰቡ መረጃዎች መነሻነት ነገሮችን በጣም ሳቢ ማራኪና አሳማኝ በሆነ መልኩ የመፍጠር ተግባር ነው ማለት እንችላለን፡፡ የፈጠራ ጽሑፍ ሀሳብንና ስሜትን ገላጭ፣ ፈጠራዊና ምናባዊ በሆነ መንገድ

ማቅረብን የሚጠይቅ በመሆኑ ከጽሑፍ ተግባራት ሁሉ በጣም ፈታኙ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህም ይመስላል ጽሕፈት የትጉሃን ስራ ነው የሚባለው፡፡ መፍጠር አስቸጋሪና ፈታኝ ቢሆንም በዚያው ልክ ደግሞ እጅግ አስደሳች ስራ ነው፡፡ መጻፍ የግላዊ ነፃነት አንድ መልክ በመሆኑ ማህበረሰቡ በወል ከተላበሰው ማንነት ይለየናል፣ ዙሪያገባችንን ያስቃኘናል፡፡ ደራሲያን ራሳቸውን ነገሮችን በግርድፉ እየተመለከቱ ከሚዋዥቁበት አለም ለመውጣት ይጽፋሉ፣ የራሳቸውን ሰላማዊ ደሴት ለመፍጠር ይጽፋሉ፡፡

## የፈጠራ ጽሑፍ ለመፃፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች

### መነቃቃት /Becoming Inspired/

ለመጻፍ ራሳችንን ካሳመንን በኋላ ቀጣዩ ተግባር የሚሆነው ነው፡፡

*የፈጠራ ጽሑፍ ለመፃፍ ከመነሳታችን በፊት፡-*

- *ለመጻፍ ራሳችንን ማሳመን*
- *የጽሑፍ ተሰጥዖዋችን ምን ላይ እንደሆነ በጽሑፍን በመሞከር መለማመድ፤*
- *ንቁና አስተዋይ መሆን፤*
- *የጠያቂነትን መንፈስ ማዳበር ነው፡፡*
- *በመቀጠልም ስለምን እንደምንጽፍ ማወቅ ወይም አስቀድመን ስለምን ወይም በምን ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ መፃፍ እንደምንፈልግ ማወቅ አለብን፡፡ ይህን በማድረጋችንም በጽሕፈት ጊዜ አንዱን ሀሳብ አንስተን ሳንጨርሰው ደግሞ ወደሌላው እየተሻገርን መጨበጫ የሌለውና ፍሬ ቢስና ዝብርቅርቅ ያለ ጽሑፍ ከመጻፍ እድንድን ምክንያት ይሆናል፡፡*
- *በፈጠራ ጽሑፍ ሒደት የተዋጣለት ጽሑፍ መፃፍ የምንችለው፡-*
    - *ስሜታችንን በተለየ ሁኔታ የሚነካን ጉዳይ ላይ ተመስርተን ስንጽፍ ነው ወይም ስሜታችን የጽሑፋችን መነሻ ሲሆን ነው፡፡*
    - *ስሜት በጥሩ ሁኔታ ወደጽሑፍ ሲቀየር አንባቢዎች በፍላጎትና በጉጉት የሚያነቡት ጽሑፍ ይፈጠራል፡፡*

ሥለዚህ ሁልጊዜ አንድን ጽሑፍ መፃፍ ከመጀመራችን በፊት ለስሜታችን ልዩ ትኩረት ሰጥተን ሥሜታችንን ማዳመጥ ይገባናል፡፡

ጽሑፍ በመጻፍ ሂደት ለመፃፍ መነሻ የሚሆኑንን ሃሳቦች ሥሜታችንን የሚነኩ ሃሳቦች በተለያየ አጋጣሚ ከተለያየ ቦታዎች ልናገኝ እንችላለን፡፡ ከእነዚህ ጉዳዮች ውስጥ ጥቂቶቹ፡-

- *ከእውነተኛ ገጠመኞች - ከልዩ ልዩ ጽሐፍት - ከሌሎች ሰዎች ገጠመኞች*
- *ከሚዲያዎች - ከታሪክ መዛግብት - ከጦርነት ታሪኮች*
- *ከፊልም - ከፍልስፍና ጽንሰ ሃሳቦች - ከልዩ ልዩ የሙያ መስክ ጽንሰ ሃሳቦች ወ.ዘ.ተ ከሁሉም በላይ ስሜት ነኪ ጉዳዮችን ከእኛው ከራሳችን ጥልቅ አስተውሎት ልናገኛቸው እንችላለን፡፡*

ይህን ሃሳብ በምሳሌ ለማስደገፍ ያህል፡-

- *ገጣሚያን በአንድ ተራ የሚባል የህይወት እንቅስቃሴ*
- *የልቦለድ ደራሲያን በነባራዊው ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ ተመርኩዘው ሊጽፉ ይችላሉ፡፡ ይህ እያንዳንዱ የእለት ተለት ህይወት እንቅስቃሴ በሆነ መንገድ ስሜታችንን ሊነካውና ለመፃፍ መነሻ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል፡፡ ስለሆነም ሁልጊዜ ንቁና አስተዋይ ተመልካች መሆን ያስፈልጋል፡፡*

ወደውጭ በዙሪያችን ወደውስጥ ደግሞ በእኛነታችን ውስጥ ባለው አለም የሚከናወኑ ነገሮችን ትኩረት ሰጥቶ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ፡-

- *በጽሑፍ ሒደት በተለይ በፈጠራ ጽሑፍ ተራ የሚባል አንድም ነገርም ሆነ ክስተት የለም፡፡ ሁሉም ነገር ሁሉም ክስተት ልዩና ድንቅ ዋጋ ያለው ነው፡፡*
- *ስለዚህ ለዝርዝርና ጥቃቅን ነገሮች ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡*
- *ከዚህ ባሻገር ዙሪያችንና ውስጣችን በምስጢራት የተሞላ በመሆኑ፣ ይህ ምንድን ነው ወይም ለምን ሆነ ብለን የመጠየቅ ልምድ ማዳበር አለብን፡፡*
- *ምስጢራዊ የሆኑ ጉዳዮችን መርምረን ለመግለጥ መሞከር፣ በውስጣችን ለሚፈጠሩ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት በጋለ ፍላጎት መንቀሳቀስ፣ ያልተለመዱ ነገሮች ሲያጋጥሙን ልዩ ትኩረት ሰጥተን ማስተዋል መልካም ነው፡፡*

ይህ ሁሉ አንድ ላይ ሆኖ ለመፃፍ የሚሆን መነሻ ሀሳብ ከማቀበሉም በላይ ጽሑፋችን በሀሳብ የበለፀገ፣ ለእውነታ የቀረበና በጣም አሳማኝ እንዲሆን ይረዳናል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ንባብ እውቀታችንን ለማስፋት የሚያስችለን ሙሉ ሰው የሚያደርገን ሌላው የሚመከር ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም በንባብ ልዩ ልዩ ዕወቀት ከማግኘታችን ባሻገር የሌሎችን ስኬታማ ስራዎች በማንበብ የስኬታቸውን ምስጢር በመለካት የእኛን የስኬት በር ማስፋት ለመጣር መንገድ ይሆነናል፡፡ ይህንን በሁሉም አይነት የፈጠራ ጽሑፍ ዘርፎች ዙርያ ልናከናውነው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ አንድን ጥሩ የሚባል የግጥም ስራ ከተለያየ አቅጣጫ ግጥሙን በመፈተሽ ለመረዳት፡-

- *የገጣሚው ስሜት ምን ላይ ያተኮረ ነው፣*
- *ጉዳዩን በምን አይነት መልኩ ተመለከተው፣*
- *ስሜቱንስ እንዴት ባለ ዘዴ አሰፈረው*
- *ግጥማዊ ብልሃቶቹ ምን ይመስላሉ*
- *የቋንቋ አጠቃቀሙ፡ምን ይመስላል፤*
- *ድምጸቱስ ምን ይመስላል የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅና በመመለስ በዚህ መነሻነት የራሳችንን ገጠመኞች መለስ ብለን መፈተሽ፡፡* በዚህ አጋጣሚ ብልጭ የሚሉ ሀሳቦች አይጠፉም፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በየጊዜው ማስታወሻ መያዝም በጠቃሚ ዘዴነት ሊታይ ይችላል፡፡ የሰው ልጅ አእምሮ በተፈጥሮው የሃሳብ ማዕበል የሚጥለቀለቅበት በመሆኑና በእዚህ ማዕበላዊ ሂደት በአእምሯችን ብቅ ከሚሉ በርካታ ጉዳዮች ውስጥ እጅግ የሚደንቁ ልሂቅ ሃሳቦች እናገኛለን፡፡ እነዚህንን በአጋጣሚ ድቅን የሚሉብንን ቅጽበታዊ ሃሳቦችን ከትበን ለማስቀረት የትም ቦታ ስንንቀሳቀስ ብዕርና

ወረቀት የመያዝ ልምድን ማዳበር ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም የሚስብና ለመፃፍ የሚያነሳሳ ነገር ስናገኝ ከመርሳታችን በፊት በአጫጭር ማስታወሻዎች መልክ ሀሳባችንን ለማስፈር እንዲረዳን ነው፡፡

አዳዲስ ሀሳቦች ከምናየው፣ ከምንሰማው፣ ከምናሸተው፣ ከምንቀምሰውና ከምንዳስሰው ነገር ጋር ተያይዘው ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በማስታወሻ የምናሰፍራቸው ነገሮች ህልሞቻችን፣ በጣም ያስደነቁን የሰዎች ንግግሮች፣ ያየናቸው ስዕሎች/ፎቶዎች… የመሳሰሉት ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ቆይተን ማስታወሻችን መለስ ብለን ስንመለከት ለመፃፍ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ርዕሰ ጉዳዮችን ልናገኝ እንችላለን፤ መፃፍ ከጀመርንም በኋላ ማጠናከሪያ የሚሆኑ ሃሳቦችን በማቀበል ማስታወሻችን ትልቅ አገልግሎት የሰጣል፡፡ ከዚህ ውጪ በመገናኛ ብዙሃን የሚቀርቡ ዜናዎች፣ ካለፈ ህይወታችን ያገኘናቸው ልምዶችና መሳሰሉት ጉዳዮች ጥሩ መነሻዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ Ramet (2007፣4-5)ትገልፃለች፡፡

**ጊዜና ቦታን መምረጥ**

በምንጽፍበት ወቅት ምቾት የሚሰጠንን ጊዜና ቦታ አስቀድመን በመምረጥ አዘውትረን ያንን ጊዜና ቦታ ለጽሑፍ ስራችን እንድንጠቀም ይመከራል፡፡ ለፈጠራ ስራ ንቁ የሆነው የአእምሯችን ክፍል የመረጥነውን ቦታና ጊዜ አንዴ ከለመደው ሁልጊዜ በዚያ ቦታና ጊዜ በተገኘን ቁጥር የመፍጠር ዝንባሌ ይኖረዋል፡፡

ብዙ ጊዜ የፈጠራ ጽሑፍ ባለሙያዎችን ገጠመኞች ስንመለከት፡-

- *አንዳንድ ደራሲያን ፀጥታን ይመርጣሉ፣*
- *ሌሎች ደግሞ የፈጠራ ሀይላቸውን ለማነቃቃት ሙዚቃ ያዳምጣሉ፣*
- *የተቀሩት ከተለያዩ ሰዎች ጋር በመሆን ልዩ ልዩ ሃሳቦችን በማንሸራሸር በውይይቱ መካከል ምርጥ የድርሰት ሀሳብ ብልጭ ይልላቸዋል፡፡*
- *እንቅልፍ ሊተኙ በተቃረቡበት ሰዓት ሀሳብ ሰለሚመጠላቸው በዚህ ወቅት አጫጭር ማስታወሻዎችን ጽፈው የሚተኙና በማለዳ ተነስተው መፃፍ የሚሆንላቸውም አሉ፡፡*
- *በሌላ ወገን ደግሞ ምንም አይነት ረብሻ የሌለበት ረጅም ጊዜን ስለሚፈልጉ የሳምንቱን የመጨረሻ ቀናት ለመፃፍ የሚመርጡ አሉ፡፡*

ቦታን በተመለከተም እንዲሁ የየደራሲው ምርጫ የተለያየ ነው፡፡

- *አንዳንዶቹ የተለዩ ህንፃዎች ወይም ቤት ውስጥ፣ ከቤትም የተለየ አንድ ክፍል ውስጥ፣ ወንበር ላይ፣ አልጋ ላይ፣ መሬት ላይ፣*
- *ጫካ ውስጥ፣*
- *ወንዝ/ሀይቅ/ባህር ዳር…*
- *ፏፏቴ ስር*
- *ለምለም ሳር ያለበት ሜዳ*
- *ቅልጥ ያለ የሰዎች ጩኸት ያለለበት አካባቢ(ምሳሌ መርካቶ)*

- *ከፍ ካለ ተራራ ላይ ወዚተ የመሳሰሉት ስፍራዎች ሊመረጡ ይችላሉ፡፡*
- *ዋናው ጉዳይ ባለተሰጥዖው ለመፃፍ የሚስማማውን ቦታና ጊዜ መምረጥ የሱ ድርሻ ነው፡፡*

አንዳንዴ ደግሞ ሁለንተናችንን በፍጹም ጸጥታ ውስጥ ከትቶ ሃሳብ ከወደውስጣችን እንደጅረት እንዲፈስ ብቻ እያዳመጥን እንድንጽፍ የሚያደርገን ጊዜና ቦታ ሊያጋጥመን ይችላል፡፡ ይህ እንግዲህ የኛ ትክክለኛ የመፃፊያ ጊዜና ቦታችን ነው ማለት ነው፡፡

**መፃፍ መጀመር**

የፈጠራ ጽሑፍ ስራ አንዴ የሚያድግ ተግባር አይደለም፡፡ በአንዴ ፍጹምነት ደረጃ አይደረስም፡፡ ይልቁንም ደግሞ ደጋግሞ መሞከር ተገቢ ነው፡፡ ደግመን ደጋግመን የምንሞክር ከሆነ፡-

- *የምናብ እና የፈጠራ አቅም ይጨምርልናል*
- *ሃሳብ የማደራጀት ችሎታችንን ከፍ ያደርግልናል፤*
- *በራስ መተማመናችንን ይጨምራል፤*
- *የተግባቦት ክሂላችንን ከፍ ይላልና ሁሌም ደግሞ ደጋግሞ መለማመድ ተገቢ ነው፡፡*

ስለዚህ የፈጠራ ጽሑፍ ተግባር ሂደት ወይም ደረጃ አለው ማለት ነው፡፡ የመጀመሪያው ደረጃ መጻፍ መጀመር ነው፡፡ መጻፍ መጀመር በተለይ ለጀማሪ ደራሲያን በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ምንም አይነት የሚፃፍ ሀሳብ ይጠፋና ባዶው ወረቀት ላይ በማፍጠጥ ብቻ ረጅም ጊዜ ሊያልፍ ይችላል፡፡ በዚህ ወቅት ሊያግዙ የሚችሉ አንዳንድ ዘዴዎች አሉ፡፡
እነዚህ ዘዴዎችም፡-

- *በቅድሚያ ወደ አእምሯችን የመጣውን ሀሳብና የሚሰማንን ስሜት ሁሉ (የአየሩ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የሰማዩ ገጽታ፣ የአፈሩ ሽታ፣ የሰዎች እንቅስቃሴ፣ የመኪኖች ድምጽ...) በጽሑፍ ለማስፈር መሞከር፡፡*
- *ወይም ይህ ብዙ የማያስኬደን ከሆነ ብዙ እንቅስቃሴ ያለበትና ሰዎች የሚበዙበት አካባቢ በመሄድ የስሜት ህዋሶቻችንን ንቁ አድርገን በቦታው እየተከናወነ ያለውን ነገር በትክክል በማስታወሻችን ላይ ለማስፈር መሞከር፤ የሰዎችን ንግግር መመዝገብ ንግግሩ ላይ ቃላትን የመጨመር፣ የመቀነስ፣ የማሻሻልና የመለወጥ ስራ መስራት፡፡*
- *ከአከባቢያችን ነባራዊ ሁኔታ ተነስተን መቼቶችንና ገፀባህሪያትን ለመፍጠር መሞከር፡፡ የፈጠራ ሂደቱን ለማቀላጠፍ ገጸባህሪያቱ ምን ይፈልጋሉ፣ ምን ይፈራሉ፣ ምን የደበቁት ምስጢር አለ፣ እነማን ናቸው፣ ስማቸው ማን ነው፣ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች መጠየቅና መልስ ለማግኘት መሞከር፡፡*

በዚህ መልኩ የተዘጋውን የሀሳብ በር ከከፈትንና ካሟሟቅን በኋላ ቀጥሎ በተደላደለ መውረጃ የሚፈሰውን በውስጣችን የተፋፋመ ሃሳብና ስሜት ወደ ቃላት በመቀየር በጥሩ ሁኔታ በጽሑፍ ለማስፈር መሞከር ነው፡፡

የምንጽፈው ነገር የአንባቢያንን ቀልብ የሚስብና በተመስጦና በደስታ የሚነበብ አይነት ከሆነ ተከታይ ስራችንም በጉጉት የሚጠበቅ ይሆናል፡፡ ይህን ለማሳካት ስሜት ላይ ማተኮር አማራጭ የሌለው መፍትሔ

ነው፡፡ በአምስቱ የስሜት ህዋሳት በኩል የሚመጣ መረጃ ላይ ተመርኩዞ የሚጻፍ ጽሑፍ የአንባቢን ቀልብ የመሳብ እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ጽሑፋችንን ከስሜታችን ጋር የተቆራኘ ለማድረግ ደግሞ የምንጽፍበት ርዕሰ ጉዳይ የምናውቀውና የምንወደው ሊሆን ይገባል፡፡ ስለምናውቀው ነገር ስንጽፍ ስራችን ቀላል ይሆናል፣ የተሸለ ነገር መፍጠርም እንችላለን፡፡

ከዚህ ባሻገር ለጽሑፉ አካሄድ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ጽሑፉ የት ላይ ተጀምሮ ወዴት ይሄዳል የት ላይስ ያልቃል የሚለው ጉዳይ በጥንቃቄ መጤን አለበት፡፡ በተጨማሪም ዝርዝር እውነታዎችን በማካተት ጽሑፉን ግልጽና ለመረዳት የማይፈትን ማድረግ መልካም ነው፡፡ ለምሳሌ ውበት ሲገለጽ በደፈናው ቆነጆ ነው/ናት ከማለት ይልቅ ለእያንዳንዱ የአካል ክፍል ትኩረት ሰጥቶ መግለጽ ያስፈልጋል፡፡

## በምንጽፍበት ወቅት ልንጠነቀቅባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

በምንጽፍበት ወቅት ልንጠነቀቅባቸው የሚገቡ ጉዳዮች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- *መፃፍ የሚገባን ስለምናውቀው ነገር መሆን አለበት፤*
- *ሀሳብ በማቅረብ ብቻ ሳይሆን በቃላት መረጣ ወቅትም መጠንቀቅ ይገባል፡፡*
- *ትርጉሙን በሚገባ የምናውቀውን ቃል መጠቀም ይኖርብናል፡፡*
- *ጽሑፋችንን ቀለል ባሉ ቃላት መጀመር ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም በከባድ ቃላት የሚጀምር ጽሑፍ ሀሳቡን ለመረዳት በሚፈጥረው ችግር የተነሳ ገና ከመነሻው አንባቢያንን ከመሳብ ይልቅ የመግፋት ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡*
- *እንግዳ የሆኑ ቃላትን በመደርደር ለጽሑፉ ክብደት ለመስጠት ከመሞከር ይልቅ ሰዎች እንዲረዱልን የፈለግነውን ነገር በቀላሉ ለማስረዳት መሞከሩ የተሻለ ነው፡፡*
- *በተቻለ መጠን ግልጽ የሆነ የአፃፃፍ ስልት መከተል፤*
- *የፈለግነውን ነገር ሳንጨምርና ሳንቀንስ ራሱን ብቻ በትክክል ለማለት መሞከር አለብን፡፡*
- *የምንጽፈው ዝርው ከሆነ በጸሑፋችን መጀመሪያ አካባቢ አጫጭር ዐ.ነገሮችን ማዘውተር፣ ምክንያቱም አጫጭር ዐ.ነገሮች በውስጣቸው የያዙትን ሀሳብ አንባቢው በቀላሉ ለማብላላት እንዲችል መንገድ ይከፍታሉ፡፡ አለፍ አለፍ ኢያልን ረጃጅም ዐ.ነገሮችን መጠቀም፡፡*
- *የምንጽፍበትን ቋንቋ ስርዓት ጠንቅቀን ማወቅና መገልገል ይገባናል፡፡*
- *ያለምንም ምክንያትና እርባና የቋንቋውን ስርዓት አለማፍረስ፤ ምክንያቱም፡- በቋንቋው መጫወት ማለትም ስርዓትና ህጉን በማፍረስ አዳዲስ ቃላትንና አገላለጾችን መፍጠር በዚህም ለጽሑፋችን ውበትን መስጠት መልዕክታችንንም ለየት ባለ መንገድ ማስተላለፍ ማለት ነው፡፡*

## 1. የፈጠራ ጽሁፍ አይነቶች

የፈጠራ ጽሑፎች በሁለት ዋና ዋና መንገድ ይከፈላሉ እነሱም፡- ኢ-ልቦለዳዊ እና ልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፎች ናቸው፡፡ እነዚህን ሁለት ዓብይ የፈጠራ ጽሑፍ ዓይነቶች ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### ኢ-ልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፎች

ኢ-ልቦዳዊ የፈጠራ ጽሑፍ እውነታን በስነጽሑፋዊ ስልቶችና ዘዴዎች ከሽኖ የሚያቀርብ የፈጠራ ጽሑፍ ዘርፍ ነው፡፡ "የኢልቦለድ ጽሑፎች ብለን የምንጠራቸው የዝርው ጽሑፍ ዓይነቶች በዓይነታቸው ብዙ በባህሪያቸውም የተለያዩ ናቸው፡፡" (ጌታቸው 2004፣266) የኢ-ልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፍ ደራሲ ቀዳሚ አላማው ልክ እንደጋዜጠኛ መረጃን ማስተላለፍ ሲሆን ይህንኑ እውነተኛ መረጃ ግን በልቦለዳዊ የአፃፃፍ ስልት ከሽኖ ያቀርባል፡፡ ኢ-ልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፍ "የፈጠራ ገጸባህሪያት የሚንቀሳቀሱበት ሳይሆን በራሱ በገሃዱ አለም ሰው ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡" (ዝኒ ከማሁ፣ 267)፡፡ በመሆኑም በደራሲው አእምሮ የተፈጠሩ ሳይሆኑ በእውነተኛው አለም የሚገኙ ታሪኮችን ያቀርብልናል፡፡ ይህም ሲባል የሚቀርቡት መረጃዎች በእውነተኛው አለም ተፈልገው ሊመሳከሩ የሚችሉ ናቸው ማለት ነው፡፡

በኢልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፍ ግላዊ የሆነ አመለካከትን ማንጸባረቅ የማይፈቅድ ቢሆንም እውነታን የተመረኮዘ አስተያየት መሰንዘር ግን ይቻላል፡፡ ኢልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፍ በምርምር የዳበረ እውነተኛ መረጃ መያዝ፣ በሚያቀርበው እውነተኛ መረጃ የአንባቢውን ትኩረት መሳብ እንዲሁም የእውነታ መሰረቱን ሳይለቅ የእውኑንና ምናባዊውን አለም ሳቢና አስደሳች በሆነ ስነጽሑፋዊ ስልት ማስተሳሰር መቻል አለበት፡፡ በዚህ ጎራ ስር የሚካተቱ በርካታ የፈጠራ ጽሑፍ አይነቶች ቢኖሩም ዋና ዋና የሚባሉትን ጥቂቶቹን ብቻ በመቀጠል በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

### ግለህይወት ታሪክ /Autobiography/

የእንግሊዝኛው ቃል autobiography የሶስት የግሪክ ቃላት ቅንጅት ሲሆን እነዚህም autos= self (ራስ/እኔነት) + bios=life (ህይወት) + graphein=to write (መፃፍ) ይሆኑና autobiography የሚለውን ቃል ይሰጣሉ ማለት ነው፡፡ የሀገራችን ዝነኛ ገጣሚ ሰይፉ መታፈሪያ autobiographyን "ኔበንተኔ" ሲል ይተረጉመዋል፡፡ (1987፣26) ነገር ግን በዚህ ሞጁል በአብዛኛው ሰው ዘንድ ታዋቂ የሆነውንና የተለመደውን "ግለህይወት ታሪክ" የሚለውን ፍቺ እንጠቀማለን፡፡

ግለህይወት ታሪክ ረጅም እድሜን ያስቆጠረ የፈጠራ ጽሑፍ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ በ3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኖረው የክርስትና ሀይማኖት አባት Augustine "Confession"ን ጽፏል፡፡ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ደግሞ የመጀመሪያው ግለህይወት ታሪክ ተደርጎ የሚወሰደው አብደላ ኢብን ቡሉኝ የተባለው ንጉስ በ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የፃፈው የህይወት ታሪክ ነው፡፡ Leonor Cordoba የተባለች ስፔናዊት ሴት ደግሞ በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንዲሁ የህይወት ታሪኳን ጽፋለች፡፡ ታላላቅ ስራዎች ተብለው

ከሚጠሩት ግለህይወት ታሪኮች መካከል በRenaissance (1556-1558) ዘመን የተፃፈውና የጣሊያናዊው Benvenuto Cellini ስራ የሆነው *Vita*=Life ይገኝበታል፡፡

በሀገራችን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በዘመናችን ከተፃፉ ግለህይወት ታሪኮች ባሻገር ወደኋላ ተጉዘን ራቅ ያለ ዘመንን የሚያጣቅሱ ግለህይወት ታሪኮችን ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለግለህይወት ታሪክ አፃፃፍም ሆነ ጠቀሜታ ከማንሳታችን በፊት ስለምንነቱ አጭር ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ግለህይወት ታሪክ የአንድ ሰው ሙሉ የህይወት ታሪክ ሲሆን የሚፃፈውም በገዛ በባለታሪኩ ነው፡፡ ስለሆነም ፋንታሁን እንግዳ ግለህይወት ታሪክ "አንድ በታሪክ የታወቀና የተደነቀ ሰው በህይወት ዘመኑ የሰራቸውን ተግባራት እና የደረሰበትን ውጣ ውረድ ሁሉ በዘመን ቅደም ተከተል እያስተካከለ ስለራሱ በገዛ ብዕሩ እያንቆለጳጰሰ ፅፎ የሚያቀርበው ጽሑፍ ነው፡፡" ሲል ይገልጸዋል፡፡ (2001፣17)

## የግለህይወት ታሪክ መገለጫ ባህሪያት

በግለህይወት ታሪክ ውስጥ የሚሰፍረው ታሪክ የሚፃፈው በራሱ በባለታሪኩ ስለሆነ በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንፃር ይተረካል ወይም ተራኪው እኔ እያለ ታሪኩን ያቀርባል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው የታሪኩ ፍሰት በፀሐፊው እውናዊ ህይወት ድርጊቶችና ሁነቶች የተከሰቱበትን ቅደም ተከተል ጠብቆ ይፃፋል፡፡ ይሁን እንጂ እያንዳንዱ በባለታሪኩ የህይወት ውጣ ውረድ ውስጥ የተከሰተ ድርጊትና ሁነት ሁሉ አይፃፍም፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት አንድ ግለሰብ ተወልዶ እስከሚሞትበት እለት ድረስ የሚከናወኑ ጉዳዮች እጅግ በርካታ በመሆናቸው ነው፡፡

> የግለ ታሪክ ደራሲው ባሳለፈው የህይወት ዘመኑ ለቁጥር የሚያታክቱ ክፉና በጎ ገጠመኞች ገጥመውት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱን ጥቃቅን የህይወት ገጠመኝና ክንውን እንዲተርክልን አይገደድም፡፡ እያንዳንዱ ሰባራ ሰንጣራ ገጠመኙን ለመፃፍ ቢነሳ ምናልባት የውቂያኖስ ውሃ እንደቀለም ተበጥብጦ ምድር እንደወረቀት ተዘርግቶ ቢሰጠው እንኳን መፃፊያ ወረቀትና ቀለም ሊበቃው አይችልም ብለን የግነት አነጋገር እስከመናገር ሊያደርሰን ይችላል፡፡ (ስብስብ 2001፣17)

ስለሆነም በባለታሪኩ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱና አሁን ላለው ማንነቱ መፈጠር አስተዋጽኦዋቸው ጠንካራ የሆኑ ጉዳዮች ብቻ ተመርጠው በታሪኩ ውስጥ ይሰፍራሉ፡፡ የባለታሪኩ ድል፣ ሽንፈት፣ መከራ፣ ደስታ፣ ሀዘን... የመሳሰሉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካተት አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ ባለታሪኩ በህይወቱ ያሳለፋቸውን ነገሮች በመመዘን፣ በእያንዳንዱ ክስተት መካከል የምክንያትና ውጤት ሰንሰለት በመገንባት፣ በህይወቱ ውስጥ የወሰናቸውን ታላላቅ ውሳኔዎች መለስ ብሎ በማየት ማንነቱን ለመቅረጽ ይጥራል፡፡

ግለሰቦች ታሪካቸውን በሚያሰፍሩበት ወቅት ጸሐፊው በህይወቱ ውስጥ የተከሰተውን እያንዳንዱን ነገር በተጨባጭ መግለጽ ስለሚያዳግተው ወይም ሙሉ ትውስታ ላይኖረው ስለሚችል፤ እጅግ ለእውነታ የቀረበ መረጃ ይዘዋል የሚባሉት ግለህይወት ታሪኮች ሳይቀሩ በተወሰነ ደረጃ ልቦለዳዊነት ሊታይባቸው ይችላል፡፡ በሌላ አባባል ጸሐፊው ያስታወሰውን አስታውሶ የቀረውን የታሪኩን ክፍል እሱ ሆኗል ብሎ በሚያስበው መንገድ ሊሞላው ይችላል ማለት ነው፡፡ ከዚህም በላይ 'እውነት' እንደየሰው አመለካከት ሊለያይ የሚችል ጽንሰ ሀሳብ በመሆኑ፤ ማንኛውም የግለህይወት ታሪክ ፀሐፊ ቢሆን በህይወቱ ውስጥ የተከሰተውን ነገር ከራሱ አተያይ አንፃር ይናገራል እንጂ ትክክለኛውን እውነት ሊያቀርብ አይችልም፡፡

በሌላም በኩል ግለህይወት ታሪክ በግለሰቡ ትዝታ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ ወይም ግለሰቡ ያስታወሰውንና ማስታወስ የፈለገውን ብቻ ስለሚጽፍ፣ የተሳሳተ መረጃ የማቀበል ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ጸሐፊው የፈለገውን ጽፎ ያልፈለገውን አስቀርቶ፣ የፃፈውንም ቢሆን ታሪኩ በተከሰተበት መልኩ ሳይሆን እሱ እንዲሆን በፈለገው መንገድ አስተካክሎ ሊያቀርበው ስለሚችል የመረጃው አስተማማኝነት ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህ ድርጊት ምናልባት ራስንና ሌሎች በታሪኩ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችን ከአደጋና ከውርደት ለመጠበቅ ሲባል ሊፈፀም ይችላል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ግን ስራው እውናዊ ከመሆን ይልቅ ወደልቦለዳዊነት እያመዘነ ይሄዳል፡፡ ስለሆነም ግለህይወት ታሪክ ሲጻፍ በተቻለ መጠን በጥሩ ሁኔታ የሚታወስና በትክክል የተከሰተ ጉዳይ ላይ ቢመሰረት መልካም ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ግለህይወት ታሪክን በተሻለ መልኩ ለመፃፍ የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦችን እንመለከታለን፡፡

### ግለህይወት ታሪክ ለመፃፍ የሚረዱ መንደርደሪያዎች

- *ለምን እንደምንጽፍ ማወቅ፡- ጥሩ ግለህይወት ታሪክ ለመፃፍ ካሰብን ምክንያታችን ፍላጎት ቢሆን ይመረጣል፡፡ የምንፅፈው የህይወት ልምዶቻችንን ለሌሎች ለማጋራት፣ አሁን ያለውን እኛነታችንን በዚህ መልኩ የቀረፁትን ሀይሎች ለመመርመርና ለመረዳት፣ ታሪካችንን ለትውልድ ለማስቀረት፣ ወይም የመፃፍ ጥማችንን ለማርካት ሊሆን ይገባዋል፡፡*
- *የተፃፉ ግለህይወት ታሪኮችን ማንበብ፡- የሌሎችን ስናነብ የራሳችንን እንዴት መፃፍ እንዳለብን ፍንጭ እናገኛለን፣ የትኞቹ የህይወታችን ገጽታዎች መነካት እንደሚገባቸው ማወቅ እንችላለን፡፡*
- *ግለህይወት ታሪካችን በዋናነት የሚያጠነጥንበትን ርዕሰ ጉዳይ መወሰን፡- ታሪካችንን በቅደም ተከተል መደርደር ብቻ በቂ አይሆንም፤ በዋናነት ለሌሎች ልናጋራው የፈለግነውን ቁምነገር ወስነን ለዚህ ጉዳይ አጽንኦት ሰጥተን ልንጽፍ ይገባል፡፡ በህይወታችን ትልቅ ቦታ የምንሰጠው ጉዳይ ፍቅር፣ ድህነት፣ ሀብት፣ ጦርነት፣ የድርሰት ስራ... ሊሆን ይችላል፡፡ ምንም ይሁን ምን ከፍተኛ ዋጋ በምንሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ታሪካችን እንዲሽከረከር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ በመሆኑ አላስፈላጊ (እምብዛም ጠቀሜታ የሌላቸውን) የታሪካችንን ክፍሎች በቀላሉ ልናስወግድ እንችላለን፡፡*
- *ትዝታዎቻችንን መፈተሽ፡- ይህን ለማድረግ ተመራጩ ዘዴ ያለፈ ህይወታችን ቅሪት የሆኑ ቁሳቁሶችን (ፎቶግራፎች፣ ደብዳቤዎች፣ የእለት ውሎ ማስታወሻዎች፣ የምንወዳቸው ዘፈኖች፣ መፃህፍት፣ ፊልሞች፣ ልብሶች...) መለስ ብሎ ማየት ነው፡፡ ይህን በምናደርግበት ጊዜ ለጽሑፋችን ግብዓት የሚሆኑ የተለያዩ ትውስታዎችን ከነስሜታቸው በቀላሉ ማምጣት እንችላለን፡፡*

- *አንባቢያንን ከግምት ውስጥ ማስገባት፡- የምንጽፈው ለራሳችን ከሆነና ሌላ ሰው አያነበውም ብለን ካሰብን ታሪካችንን በፈለግነው መንገድ ልንጽፈው እንችላለን፡፡ ነገር ግን ለአንባቢያን የሚቀርብ ስራ ከሆነ፣ እኛ የምናውቀውን ሁሉ አንባቢዎቻችን ኢያውቁምና ግልጽነቱ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡*
- *ታማኝ መሆን፡- ግለህይወት ታሪካችንን ስንጽፍ ልናዝን፣ ልንፀፀት ወይም ልናፍር አይገባም፡፡ የምንጽፈው ስላለፈ የህይወታችን ክንውን ከመሆኑም በላይ ለንባብ ልናበቃው ስንወስን ሌሎች ከኔ የህይወት ልምድ ይማራሉ ወይም ይጠቀማሉ ብለን ስለሆነ እውነታውን በትክክል ልናሰፍር ይገባል፡፡*

በአጠቃላይ ግለህይወት ታሪክ ለመፃፍ ሲታሰብ ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት እጅግ ጠቀሜታ አለው፡፡ በሀገራችን ተጽፈው ለንባብ ከበቁ ግለህይወት ታሪኮች መካከል የታዋቂዎቹ ደራሲያን የመንግስቱ ለማ ደማሙ ብዕረኛ እና የማሞ ውድነህ የደረስኩበት የተሰኙ ግለህይወት ታሪኮች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## የህይወት ታሪክ

የህይወት ታሪክ መፃፍ የጀመረው በጥንታዊው ዘመን ቢሆንም በጣም የተስፋፋውና የታወቀው ግን በመካከለኛው ዘመን ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ የህይወት ታሪኮች ምናልባትም በቀብር ስነስርዓት ላይ የሚነበቡና በመቃብር ስፍራ የሚፃፉ አጫጭር የግለሰቦች ታሪኮች ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ በሀገራችን ገድሎች ለህይወት ታሪክ እንደፈርጅ ቀዳጅ ስራዎች ሊታዩ ይችላሉ፡፡

የህይወት ታሪክ የአንድ ግለሰብ የሙሉ ጊዜ የህይወት ውጣ ውረድ ገለፃ ወይም ዘገባ ነው፡፡ የህይወት ታሪክ የግለሰቡን ልደት፣ ሞት፣ ስራ፣ ማህበራዊ ህይወትና የመሳሰሉትን ሁሉ የሚያካትት ሲሆን በተጨማሪም ግለሰቡ እንዚህን በህይወቱ ያጋጠሙትን ክስተቶች እንዴት እንዳስተናገዳቸው ይገልፃል፡፡ የሚፃፈውም ከባለታሪኩ ውጪ በሆነ አካል ነው፡፡

የህይወት ታሪክ በጥቂት ዐነገሮች ሊያልቅ ወይም አንድና ከዚያ በላይ መፃህፍት ሆኖ ተዘርዝሮ ሊፃፍ ይችላል፡፡ አጫጭር የህይወት ታሪኮች በአንድ ግለሰብ ታሪክ ውስጥ መሰረታዊ የሆኑ ነገሮችን እንዲሁም ታሪኩ ዋጋ እንዲኖረው ያደረጉ ምክንያቶችን ብቻ ባጭሩ ጠቅሰው ሲያበቁ ረጃጅሞቹ ደግሞ እነዚህን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ዝርዝር ጉዳዮችን አካተው የተስፋፋ ትረካ ያቀርባሉ፡፡ የህይወት ታሪክ ሲፃፍ ታሪኩ የሚፃፍለት ግለሰብ ወይም የዘመዶቹ ፍቃድና ትብብር አንዳንዴም ተሳትፎ ያስፈልጋል፡፡

የህይወት ታሪክ ጸሐፊ የባለታሪኩን የህይወት ጉዞ ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር እየመዘዘ ያቀርባል፡፡ በዚህ መሰረትነት ላይም የሰውየውን ማንነት (peresonality) ለመተንተን ይሞክራል፡፡ የህይወት ታሪኮች ፀሐፊዎች በግለሰቦች ህይወት ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶችን በመተንተን ክስተቶቹ እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት ያመላክታሉ፣ ምስጢራትን ለመፍታት ይሞክራሉ፣ የታሪኩን ጠቀሜታ አስመልክቶ አቋማቸውን ይገልፃሉ፣ ይከራከራሉ…ወዘተ፡፡

የህይወት ታሪኮች አብዛኛውን ጊዜ በታዋቂ ሰዎች ህይወት ዙሪያ ነው የሚፃፉት፣ ነገር ግን የተራ ግለሰብ የህይወት ታሪክ ስለአንድ የተወሰነ ጊዜና ቦታ ብዙ ሊነግረን ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የህይወት ታሪክ የሚፃፍላቸው ሰዎች በዚህ ምድር ኖረው ያለፉ ቢሆንም በህይወት እያሉ ታሪካቸው የተፃፈላቸው ግለሰቦችም አሉ፡፡

## *የህይወት ታሪክ ለመፃፍ የሚረዱ መንደርደሪያዎች*

- *አስቀድሞ ታሪኩን የምንጽፍለትን ሰው መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ምርጫችን በተለያዩ ምክንያቶች ላይ ሊመሰረት ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ የሀገር ጀግና ወይም ተወዳጅ ድምጻዊ አሊያም ታዋቂ ደራሲ ስለሆነ ታሪኩን ልንጽፍለት እንፈልግ ይሆናል፡፡ ምክንያታችን ምንም ሆነ ምን ግን ታሪኩ መፃፉ አንዳች ፋይዳ ይኖረዋል ብለን የምናምንበትን ግለሰብ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡*
- *አንድ ጊዜ የታሪካችንን ባለቤት ከመረጥን በኋላ ስለግለሰቡ ህይወት መሰረታዊ የሆኑ እውነታዎችን ማፈላለግ መቀጠል አለብን፡፡*
- *ከግለሰቡ ህይወት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቦታዎችን በመጎብኘት (እነዚህ ቦታዎች ግለሰቡ የተወለደበት፣ የሞተበት፣ አደጋ ላይ የወደቀበት… ሊሆኑ ይችላሉ)፣ እሱ ያየውን ነገር ራሳችንን በእርሱ ቦታ በማስቀመጥ ለማየት በመሞከር፣ እሱ የተሰማውን ነገር እኛም እንዲሰማን በምናብ ርቀን በመጓዝ… መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡ ግለሰቡ በዚህ ምድር ሲኖር ትኩረቱን/ቀልቡን ይስበው የነበረው ጉዳይ ምን እንደነበርና ለምን እንደሆነ ማወቅ፣ በኖረበት ዘመንም የነበረው አጠቃላይ የህይወት እንቅስቃሴ ምን ይመስል እንደነበር ለመመርመር መጣር ያስፈልጋል፡፡*
- *በቂ መረጃ የያዝን መስሎ ሲሰማን ቀጣዩ የማደራጀት ስራ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱን ማግኘት የቻልነውን መረጃ በመመዝገብ የሰበሰብናቸውን መረጃዎች እርስበርስ የሚያስተሳስራቸው አንዳች ስርዓት ለመፈለግ ጥረት ማድረግ አለብን፡፡*
- *ተደጋግመው የሚመጡ ክስተቶች ካሉ ትኩረት ሰጥቶ በመመርመርና በግለሰቡ ህይወት ውስጥ ወሳኝ የሆኑ እንደ ስኬት፣ ውድቀት፣ ሀዘን፣ ደስታ፣ ህመም ያሉ ሁነቶች ላይ በማተኮር አንዳች ትርጉም ለማግኘት መጣር፡፡ በዚህ ሁኔታ መረጃችንን ካደራጀን በኋላ ጽሑፋችን የመጨረሻውን ቅርጽ እንዲይዝ እናደርጋለን፡፡*

## የእለት ውሎ ማስታወሻ (Diary)

የእለት ውሎ ማስታወሻ በእጅ ጽሑፍ የሰፈረና በጊዜ ቅደም ተከተል የተደራጀ አንድ ግለሰብ ለራሱ የሚጽፈው የእያንዳንዱ ቀን አሊያም አልፎ አልፎ ያሉ ቀናት የውሎ ሁኔታ ዘገባ ነው፡፡

የውሎ ማስታወሻ የአንድን ግለሰብ፡-

- *ገጠመኞች፣*
- *ሀሳቦችና ስሜቶች እንዲሁም*
- *በተለያዩ ክስተቶችና ሁኔታዎች ላይ ያለውን አመለካከት ወይም አስተያየት ሊያካትት ይችላል፡፡*

- *ለመታተም ወይም ለአንባቢ ለማቅረብ ተብሎ የሚፃፍ ባይሆንም ግለህይወት ታሪኮችና የህይወት ታሪኮች በሚፃፉበት ወቅት አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡ አሁን አሁን ግን አንድ ቀን አሳትመዋለሁ የሚል ሀሳብ ይዘው የውሎ ማስታወሻ የሚጽፉ ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡*

በሥነ ጽሑፍ ታሪክ ሂደት የውሎ ማስታወሻ ረጅም እድሜን ያስቆጠረ የፈጠራ ጽሑፍ ዘር ነው፡፡ ለዚህም እንደማስረጃ "To my self" የተሰኘውና በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሮማው ገዢ Marcus Aurelius በግሪክኛ ቋንቋ የተፃፈውን የውሎ ማስታወሻ እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከዚህ በኋላ በመካከለኛው ዘመን ይበልጥ እየተስፋፋና በብዙዎች ዘንድ እየታወቀ ሄዷል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1908 ዓ.ም. Smythson የተባለ ካምፓኒ የመጀመሪያውን ቀላል የውሎ ማስታወሻ ደብተር አምርቶ ለገበያ አብቅቷል፡፡ Diary የሚለው ቃልም ለተፃፈው ጽሑፍም ለመፃፊያ ደብተሩም መጠሪያነት ያገለግላል(Honey፣2003)፡፡

ከዘመናዊው የውሎ ማስታወሻ ጎራ ከሚካተቱትና በጣም ታዋቂ ከሆኑት የውሎ ማስታወሻዎች መካከል የወጣቷ Anne Frank ማስታወሻ ይገኝበታል፡፡ ይህች ልጅ ማስታወሻውን የፃፈችው Amsterdam በጀርመኖች ቁጥጥር ስር በነበረችበት ወቅት ከአባቷና ከሌሎች ቤተሰቦቿ ጋር በድብቅ በምትኖርበት ስፍራ ሆና ነበር፡፡ ከጦርነቱ በኋላ (በ1940ዎቹ) አባቷ Otto Frank ልጁ የፃፈችውን ማስታወሻ በማርታት ለህትመት አብቅቶታል፡፡ (Massotty,2004)

## የእለት ውሎ ማስታወሻ አፃፃፍ

የእለት ውሎ ማስታወሻን የምንጽፈው፡-

- *ሌሎች ሲጽፉ ስላየን ሳይሆን መፃፍ ስላሰኘንና ማለት የምንፈልገው ነገር በውስጣችን ስላለ መሆን አለበት፡፡*
- *በፍላጎት መፃፍ የመፃፍ ሂደቱን አስደሳችና አዝናኝ ከማድረጉም በላይ የምንጽፈው ነገር ውብና ፍሬ ያለው እንዲሆን ይረዳል፡፡*
- *በተጨማሪም የውሎ ማስታወሻ የግድ በየቀኑ መፃፍ ስለሌለበት በየቀኑ ለመፃፍ በመሞከር ራሳችንን ማስጨነቅ የለብንም፡፡ በቀኑ ውስጥ የተፈፀመውን እያንዳንዱን ድርጊት ለመፃፍ ጥረት ማድረግም አይጠበቅብንም፡፡ ይልቁንም እንዲህ ያለው ተግባር ማስታወሻችንን አሰልቺ ሊያደርገው ከመቻሉም በላይ እኛንም ከፍተኛ ጉልበት፣ ጊዜ፣ ትእግስት እንዲሁም የጽህፈት መሳሪያዎች ሊጠይቀን ይችላል፡፡*
- *በሌላም በኩል የምንጽፈው ለራሳችን ስለሆነ ማስታወሻችን ከሰዋሰው አንፃር ትክክል መሆኑ ወይም አለመሆኑ፣ የሌሎችን ትኩረት ሊስብ መቻሉ ወይም አለመቻሉ፣ በየእለቱ መፃፉ ወይም አልፎ አልፎ መፃፉ... ሊያስጨንቀን አይገባም፡፡*
- *ስለሆነም ቀደም ሲል እንደተገለፀው የመፃፍ ስሜት ሲኖረን ወይም ያልተለመደ ክስተት በህይወታችን ውስጥ ሲያጋጥመን መጠቀሱ አስፈላጊ ነው ብለን የምናስበውን ክፍል ብቻ እየመረጥን በፈለግነው መንገድ መፃፍ እንችላለን ማለት ነው፡፡*
- *በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተራኪ መፃፍ አለበት፡፡*
- *በማስታወሻው ላይ የሚሰፍረው እያንዳንዱ ድርጊትና ሁኔት የተከናወነበት ቀንና ሰዓት ቢጠቀስ መልካም ነው፡፡ ይህ ያስፈለገበት ምክንያት ምናልባት ማስታወሻው የሚታተምበት አጋጣሚ ቢፈጠር አሊያም ለግለህይወት ታሪክ ወይም ለህይወት ታሪክ ማዳበሪያነት ቢፈለግ የተሟላ መረጃ ይዞ እንዲገኝ ለማድረግ ነው፡፡*
- *ከዚህ በላይ ግን የጻፈው ግለሰብ ትዝታዎቹን ወደኋላ ሄዶ መቃኘት ቢፈልግ ማስታወሻውን በሚያነብበት ጊዜ የቀኑና ሰዓቱ መገኘት ትዝታውን ሙሉ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡*
- *ቀኑ ሲጀምርና ሲገባደድ ያሉት ጊዜያት የእለት ውሎ ማስታወሻን ለመፃፍ ተመራጭ ናቸው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ጠዋት ላይ የሚሰማንን ስሜትና ከስሜታችን ተነስተን በዚያ ቀን ምን ሊያጋጥመን እንደሚችል ወይም ቀኑን እንዴት ልናሳልፈው እንደምንችል ለመተንበይ (እዚህ ላይ ሌሊት በህልማችን ያየነውንም ማካተት እንችላለን)፣ ማታ ደግሞ የጠዋቱን ትንበያችንን ከቀኑ ውሏችን ጋር በማጣመር አዋዋላችንን ጠቅለል አድርገን ለመፃፍ ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥርልን ነው፡፡*

- *በእለት ውሏችን ውስጥ ከተከናወኑ ድርጊቶችና ሁነቶች መካከል ለመፃፍ የመረጥናቸውን በዝርዝር ማስፈር ያስፈልጋል፡፡ ጉዳዩ የተከናወነበት ቦታ ገጽታ፣ የአየሩ ሁኔታ፣ የሰዎች እንቅስቃሴ፣ የእኛ አለባበስ፣ የተሰማን ስሜት የመሳሰሉት ጉዳዮች መስፈር አለባቸው፡፡ ማስታወሻው ታሪካዊ ቦታዎች ላይ የተፈፀመን ድርጊት የሚያትት ከሆነም ስለቦታው ታሪክ ጥቂት መናገር ጠቃሚ ነው፡፡ ይህን ማድረግ ምናባችንን በሰፊው እንድንጠቀም እድል ከመስጠቱም በላይ ትውስታውን ከነሙሉ ስሜቱ ከትቦ ለማስቀረት ይረዳል፡፡ በዚህ መልኩ አደራጅተን በማስታወሻችን ላይ የምናሰፍረው መረጃ እውነት ብቻ መሆን አለበት፡፡ አለዚያ ግን የእለት ውሎ ማስታወሻን አላማ በመዘንጋት ራስን መዋሸትን የመሰለ ከባድ ምስቅልቅል ውስጥ እንገባለን፡፡*
- *በእያንዳንዱ እለት ለምንጽፈው ማስታወሻ ተስማሚና ገላጭ የሆነ ርዕስ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ማስታወሻችንን መለስ ብለን በምናይበት ወቅት ርዕሱን ብቻ በማንበብ በምን ጉዳይ ዙሪያ እንደተፃፈ ለማወቅ ያስችለናል፡፡ በተመረጠው ርዕስ ስር የሚሰፍረውን ሃሳብ በተመለከተም ስሜታችንን ሁልጊዜ በጽሑፍ ብቻ ማስፈር አይጠበቅብንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ የራሳችንን ምስል መሳል እንችላለን (ስናዝን፣ ስንቆጣ፣ ስናለቅስ፣ ስንስቅ...) - መብዛት ግን የለበትም፡፡ (Honey፣2003)*
- *የአፃፃፍ ስልታችንንም ቢሆን በየጊዜው መቀያየር እንችላለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ በዝርው ሌላ ጊዜ ደግሞ በግጥም ልንፅፍ እንችላለን፤ በፅሎት መልክ ስሜታችንን ማስፈር የተሻለ መስሎ ከተሰማንም ይህንኑ ማድረግ እንችላለን፡፡ የየእለቱን ማስታወሻ ጽፈን ስንጨርስ ፊርማችንን ብናስቀምጥ መልካም ነው፤ ወደፊት እኛ ካለፍን በኋላ የሚያየው ሰው ቢኖር የኛነቱን ለማረጋገጥ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ግን አንድ ጥንቃቄ ልናደርግበት የሚገባ ጉዳይ አለ፡፡ በውሎ ማስታወሻችን ላይ የምናሰፍረው ሃሳብ በጣም ግላዊ ስለሆነ በምንጽፍበት ወቅት ብቻችንን ብንሆን ይመረጣል፤ የማስታወሻ ደብተራችንንም ቢሆን በድብቅ ማስቀመጥ አለብን፡፡ ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ ማስታወሻችንን በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ካዩት የኛም ሆነ የነሱ ስሜት የመጎዳት እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡*
- *የምንጽፍበት ወረቀትና ብእር ጥራት ያለው ሊሆን ይገባዋል፡፡ የማስታወሻ ደብተራችንን ሽፋን ላይ ስዕል በመሳል፣ ፎቶ በመለጠፍ ወይም ሌሎች ዲዛይኖችን በመስራት ማስጌጥ እንችላለን፡፡ ውስጠኛው ክፍል ላይም ከምንጽፈው ነገር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አንዳንድ ቀለል ያሉ ቁሳቁሶች በየገፁ ማስገባት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ የፊልም ቲኬት፣ የደረቀ የአበባ ቅጠል፣ ፎቶዎች... ወዘተ፡፡*

በዚህ መልኩ የተዘጋጀ ማስታወሻ ለአይን የሚማርክ ከመሆኑም በላይ የሚፈጥረው ትዝታ ብርቱ ነው፡፡ በዚህ መልኩ አሳምረን ያዘጋጀነውን ማስታወሻችንን በስም መጥራት መልመድ መልካም ነው፡፡ ለምሳሌ የየእለቱን ማስታወሻ ስንጽፍ "ውድ ጓደኛዬ" ብለን መጀመር እንችላለን፡፡ ይህን ማድረጋችን በውስጣችን የልብ ጓደኞችንን የማዋየት አይነት ስሜት እንዲፈጠርና ነፃና ግልፅ ሆነን ለመፃፍ እንድንችል ይረዳናል፡፡ ዝነኛዋ Anne የማስታወሻ ደብተሯን "Kitty" ብላ ትጠራ ነበር(Massotty,2004)፡፡

**የእለት ውሎ ማስታወሻን መፃፍ ጠቀሜታ**

የእለት ውሎ ማታወሻን መፃፍ ከምንም በላይ፡-

- *ለራሳችን ጊዜ ለመስጠትና ራሳችንን ለመግለጽ ያስችለናል፡፡*
- *በልባችን ታጭቀ የሚያስጨንቀንን ሃሳብና ስሜት ለማስታወሻችን በማዋየት ራሳችንን ማከም እንችላለን፡፡ መፃፍ ህክምና ነው፤ የታመቁ ስሜቶችን የምናስተነፍስበት ቀዳዳ በመፍጠር እፎይታን፣ ሰላምንና ጤናን ሊያስገኝ ይችላል፡፡ ስለዚህ በማስታወሻችን ላይ የምናሰፍረው ሃሳብ ለእኛነታችን ታላቅ ስጦታ ይሆናል፡፡*
- *ከዚህም በላይ የእለት ውሎ ማታወሻን መፃፍ ያለፈ ህይወታችንን መለስ ብለን ለማየትና በትዝታ ለመዝናናት፣ ስለእኛነታችንም የተሻለ ግንዛቤን ለማግኘት ጥሩ መንገድ ነው፡፡*
- *ከዚህ ውጪ ግን የፈጠራ ጽሁፍ ችሎታን ለማዳበር የሚጠቅም ተሞክሮ ሊሆን ይችላል፡፡*

## ***ወግ***(Essay)

የእንግሊዝኛው ቃል (Essay) Essayer ከሚለው የፈረንሳይኛ ቃል የመጣ ሲሆን "to try" or "to attempt" (መሞከር) የሚል ትርጉም አለው፡፡ ስለዚህ የእንግሊዝኛው (Essay) "trial" or "an attempt" (ሙከራ) ማለት ይሆናል፡፡ ፈረንሳዊው Michel Montaigne በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ቃሉን ለፃፋቸው ልዩ ልዩ ጽሑፎች መጠሪያነት ተጠቅሞበታል፡፡ ይህ ደራሲ ቃሉን የተጠቀመው የጽሑፍ ስራዎቹ ሀሳቡን በጽሑፍ ለማስፈር የተደረጉ ሙከራዎች መሆናቸውን ለማጠየቅ ነበር፡፡ የአማርኛው

"ወግ" የእንግሊዝናውን "Essay" ለመተካት የተገለገልንበት ቃል ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ደበበ ሰይፉ እንደተጠቀሙት በደራሲ መስፍን ሀብተማርያም የቡናቤት ስዕሎች እና ሌሎችም ወጎች መጽሐፍ ላይ "ማለፊያ ምዕራፍ" በሚለው ርዕስ ስር ተጠቅሷል፡፡ ነገር ግን ቃሉ የእንግሊዝኛው "Essay" የያዘውን ሀሳብ በከፊል እንጂ በሙሉ እንደማይገልጽ ራሳቸው ደበበ መናገራቸው ይታወቃል፡፡

> *...በሀገራችን የወግ የስነጽሑፍ ስራዎች አሉን፡፡ ሆኖም በጥቅሉ እስከ ዛሬም ስም አላወጣንላቸውም፤ በደምሳሳው እንለያቸው እንጂ፣ በቤተሰብ ጠገጋቸው ገናም መጠሪያ አልሰጠናቸውም፡፡ የስነጽሑፍ ታሪክ፣ ኂስ፣ ዲስፕሊን በድምሩም ባህል እያደገ ሲሄድ ደግሞ፣ በነቂስና በድምር ስማቸውን ልናውቃቸው ግድ ይሆንብናል፡፡*
>
> *እኔውም የፈረንጅኛውን ቃል Essay የሚተካ የአማርኛ አቻ ስፈላልግ ብሰነብትም፣ በሚገባኝ ምክንያት ግን፣ ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም፡፡*
>
> *...ፍለጋዬን በሌላ መንገድ በመቀጠል ከEssay ወደ Informal Essay ሄድኩ፡፡ መስፍን በዚህ መጽሐፍ የሰበሰባቸው Informal Essay የሚባሉትን ነው፡፡ ለInformal Essay "ወግ" ተገቢ አቻ ቃል ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ (የቡና ቤት ስዕሎች፣ 1999)*

የደበበ ገለፃ "ኢሴይ" የሚለው ቃል ወደፊት በዚህ ክፍል እንደምናየው መደበኛና ኢ-መደበኛ የተባሉ ሁለት ጎራዎችን አካቶ የያዘ ቃል በመሆኑ "ወግ" የሚለው ቃል በብቃት ሊወክል የሚችለው ከሁለቱ አንዳቸውን ማለትም ኢ-መደበኛ የሆነውን ብቻ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ነገር ግን የማንኛውም ወግ መነሻ ነባራዊ እውነታ ይሁን እንጅ እውነታው በወግ መልክ በሚቀርብበት ጊዜ አንዳንድ ነገሮች በፈጠራ ተጨምረውበት ወይም ተቀንሰውበት በመሆኑ "ወግ" ፈጠራንም እውነታንም በአንድነት አጣምሮ የያዘ ቃል መሆኑንና መደበኛውንም ኢመደበኛውንም የ"ኢሴይ" አይነት በብቃት ሊወክልልን እንደሚችል ፋንታሁን እንግዳ ያስረዳል፡፡ (ስብስብ 2001፣8) በዚህ ሞጁል ውስጥም ቢሆን "ኢሴይ" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ለመተካት የምንገለገልበት ይህንኑ የአማርኛ ቃል (ወግ) ይሆናል፡፡

ወግ በአንድ በተወሰነ ጭብጥ ወይም ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትኩረቱን አድርጎ በዝርው ተጽፎ የሚቀርብ የጽሑፍ አይነት ነው፡፡ ወግ ስነጽሑፋዊ ሂሶች፣ ምሁራዊ ክርክሮች፣ የእለት ተእለት ህይወት ምልከታዎች፣ ትዝታዎች የግለሰቦች አመለካከቶችና መሰል ጽሑፎችን ሁሉ ያካትታል፡፡ በወግ ሊዳሰሱ የሚችሉ ርዕሰ ጉዳዮች ቁጥር እጅግ በርካታ ከመሆናቸው የተነሳ የወግ አይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ገላጭ፣ አከራካሪ፣ ሂሳዊ፣ ህይወት ታሪካዊ፣ ጉዟዊ፣ ንጽጽራዊ፣ ተራኪ፣ ቀልድ አዘል፣ ህሊናዊ፣ ነባራዊ፣ ታሪካዊ፣ ምርምራዊ... ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ (ዝኒ ከማሁ፣ 9)፡፡ በጥቅሉ ወግ ማንኛውንም ጉዳይ አስመልክቶ ሁሉንም ነገር አጠር ባለ መልኩ ለማለት የሚያስችል የፈጠራ ጽሑፍ ዘር ነው፡፡

## የወግ ዓይነቶች

የወግ አይነቶች በሙሉ፡-

- *ምናባዊና*
- *ኢ-ምናባዊ የስነጽሑፍ ዝርያዎችን መሰረት በማድረግ፡-*
    - *መደበኛ (ኢ-ምናባዊ) ወግ "Formal Essay" እና*
    - *ኢ-መደበኛ (ምናባዊ) ወግ "Informal Essay" ተብለው በሁለት ትላልቅ ጎራዎች ይከፈላሉ፡፡*

## መደበኛ ወግ (Formal Essay)

መደበኛ ወግ ትኩረቱን ትምህርት ሰጪ ነጥቦች ላይ አድርጎ የሚፃፍ ሲሆን፡-

- *እንደ ታሪክ፣ - እምነት፣ - ፍልስፍና፣ ስኑ ህይወት፣ - ምጣኔ ሀብት፣ - ፍትህ፣ - ስነጽሑፋዊ ሂስና የመሳሰሉት ተጨባጭ ቁምነገሮች ላይ በመመስረት መረጃን ይሰጣል፡፡*

ጌታቸው በለጠ “Formal Essay” ለሚለው የእንግሊዝኛ ስያሜ “መደበኛ ኢልቦለድ” የአማርኛ አቻው ነው ይላል፡፡ ከዚህ በመነሳትም መደበኛ ወግ ከፈጠራ ጽሑፎች ጎራ መመደብ እንደማይገባው ይገልፃል፡፡ ለዚህም በዋና ምክንያትነት ያነሳው ነጥብ የቋንቋ አጠቃቀምን ሲሆን በዚህ ዙሪያ የሚከተለውን ሃሳብ አስፍሯል፡፡

> *የመደበኛ ኢልቦለድ ጽሑፎች የቋንቋ አጠቃቀም እንደ ፈጠራ ጽሑፎች በዘይቤዎች የበለጸገ፣ በአገላለጽ የተራቀቀ ወይንም የመጠቀ ዓይነት አይደለም፡፡ ዋናውና መሠረታዊ የመደበኛ ኢልቦለድ ጽሑፎች ትኩረት መልእክቱን በአግባቡ ማድረሱ ላይ ነው፡፡ መራቀቅ፣ ዙሪያ ጥምጥም፣ ቃላትን ማሽሞንሞንና “ለምድራዊው አንባቢ ጽሑፉን ጨረቃ ላይ ማንጠልጠል” የመደበኛ ኢልቦለድ ጽሑፎች ባሕርይ አይደለም፡፡ (2004፣267)*

ይሁን እንጂ ቀደም ሲል በምእራፍ አንድ ትምህርታችን ከልቦለድ ውጪ የሆኑ ጽሑፎች የፈጠራ ጽሑፍ ውስጥ የሚመደቡበት አጋጣሚ ሰፊ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ የቋንቋ አጠቃቀም ደረጃው ከልቦለዳዊ ጽሑፎች ጋር የሚስተካከል ነው ባይባልም ራሱን የቻለ ስነጽሑፋዊ ዋጋ እንዳለው ግን አይካድም፡፡ በእውነታ ላይ ተመስርተው ተጽፈው ነገር ግን የቋንቋ አጠቃቀምን ጨምሮ ሌሎች ስነጽሑፋዊ ለዛና ውበትን ተላብሰው የምናገኛቸውና የፈጠራ ጽሑፎች ብለን እንድንጠራቸው የሚያስገድዱን ጽሑፎችም በርካታ ናቸው፡፡ ይህንን ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ ፋንታሁን እንግዳ የሚከተለውን ሀሳብ አስፍሯል፡፡

> *የመደበኛም እንበለው የኢ-መደበኛ ወጎች አንድ ከሚያደርጋቸው ነጥቦች አንዱ የቋንቋ አጠቃቀም ነው፡፡ ሁለቱም ወጎች ገለጻዎችን፣ ጥቅሶችን እና ዘይቤአዊ ቋንቋዎችን አዘውትረው ይጠቀማሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር በእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚካተቱ ሃረጎች ሃይል ያላቸው እና ከግጥም ስራ ጋር ልናመሳስላቸው ባይቻለንም እንኳን የራሳቸው የሆነ ምት ያለው ቋንቋ መጠቀም ያዘወትራሉ፡፡ በአቀራረብ ረገድ ይህን የመሰለ ተመሳስሎ ይኑራቸው እንጂ ጥቅም ላይ የሚያውሉት ቋንቋ ደረጃው መለያየቱ የማይቀር ነው፡፡ (2001፣14)*

መደበኛ ወግ በነባራዊው ዓለም ላይ ተመስርቶ ተጨባጭ የሆነ መረጃን በመስጠት ላይ ያተኩራል፡፡ ስለዚህ የመደበኛ ወጎች አላማ ማስተማር ውይም ማሳወቅ ነው ማለት ነው፡፡ በመደበኛ ወጎች ውስጥ የሚቀርበው መረጃ ማንም ሰው በሚያውቀው እንዲሁም የጋራ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ያነጣጠረ ሲሆን፣ ተጨባጭነት ባለው መንገድ ተደራጅቶ ይቀርባል፡፡ ይህም በመሆኑ ግላዊ የሆኑ ስሜቶችና ገጠመኞች ላይ የመመስረት እድሉ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ “የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ገጽታ” በሚል ርዕስ የሚፃፍ መደበኛ ወግ ጸሐፊው ግላዊ ጉዳዮቹን እንዲያካትት አምብዛም እድል አይሰጠውም፡፡

## ኢ-መደበኛ ወግ (Informal Essay)

ይህንን የስነጽሑፍ ዘውግ ጌታቸው በለጠ *"የወግ ጽሑፍ" አንዳንድ ጊዜ ደግሞ "ኢ-መደበኛ ኢ-ልቦለድ"* እያለ ይጠራዋል፡፡ የኢ-መደበኛ ወግ መነሻ ሀሳቦች ቁጥር ብዙ ቢሆኑም፡-

- *እንደመደበኛ ወግ ግን ክብደት የላቸውም፡፡*
- *ዋነኛ አላማው ማዝናናት ነው፡፡*
- *በጣም ቀላል ከሆነ ርዕሰ ጉዳይ በመነሳት በምናብ ረዳትነት ሀሳቡን እያጎለበተ ማቅረብ የኢ-መደበኛ ወግ አይነተኛ ባህሪ ነው፡፡*
- *በአብዛኛው በአንደኛ መደብ ነጠላ ወይም ብዙ ቁጥር ተራኪ የሚጻፍ ሲሆን ጸሐፊው ራሱን እና አብረውት ያሉ ሰዎችን በሚጽፈው ጽሑፍ ውስጥ እማኝ በማድረግ ያስገባል፡፡*
- *ወጉንም የሚየቀርበው እኔ ወይም እኛ እያለ ስለሆነ የግል ፍላጎቱን፣ ስሜቱንና ምኞቱን ከማውራት አይዘልም፡፡*
- *በዚህም የተነሳ በኢ-መደበኛ ወግ የሚቀርበው ሀሳብ ከእውነታዊነቱ ይልቅ በፈጠራነቱ ተቀባይነትን ያገኛል፡፡*

ከላይ የኢ-መደበኛ ወግ ዋነኛ አላማ ማዝናናት ነው ተብሏል፡፡ የሚያስገርሙና ሳቅ የሚያጭሩ ድርጊቶችን በተሸሞነሞነ የአተራረክና አወጋግ ስልት ይዞ ሲቀርብ አእምሮን ዘና ማድረጉ ከፍ ሲልም ማስፈገጉ አይቀርም፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን በኢ-መደበኛ ወጎች ውስጥ የትዝብት ወይም የምጸት ድምጸት መኖሩ የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ በአዝናኝ ገለፃዎች የተሞላ ትችት ነው ልንለው እንችላለን፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች በአንድነት ሆነው የኢ-መደበኛ ወግ ጽሑፍ ከጅማሬው እስከፍፃሜው ድረስ የአንባቢን ቀልብ ሰብስቦ የመያዝ ሀይል እንዲኖረው አስችለውታል፡፡ ሃሳቡን በተጨባጭ ምሳሌ ለማየት የሚከተለውን *የቡናቤት ስዕሎችና ሌሎችም ወጎች* ከተሰኘው የመስፍን ሀብተማርያም ስራ ላይ የተወሰደውን ቅንጫቢ ወግ እንመልከት፡፡

> *… ሠዓሊ አይደለሁም፡፡ ትንሽም ልምክር ብል ዱሮ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመድኩትን ባለ አራት እግር ጠረጴዛ ነው እምሥለው፡፡ ሆኖም አንድን ሥዕል ማየት ብቻ ሳይሆን ውበቱንና መልእክቱን ማስተዋል፤ በአጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሠረት መተቸት - ደስ ይለኛል፡፡ ሙያው ባይኖረኝም አንዳች እርካታ አገኝበታለሁ፡፡ ከዚህ በመነሳት ስለ ቡና ቤት ሥዕሎች አንዳንድ የመሰሉኝን ነገሮች ለመናገር እሞክራለሁ፡፡*
>
> *… ሥዕል በጣም እወዳለሁ፤ ሠዓሊዎችንም አደንቃለሁ፡፡ "ለሥዕል ከፍ ያለ ስሜት እያለኝ ለምን ሠዓሊ አልሆንኩም" ብዬ የጠየቅኩት አንድ ወዳጄ፤ "በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል አስተማሪዎች ስላላጋተሙህ ይሆናል" ብሎኝ ነበር፡፡ … ነገሩ የሚያስኬድ ይመስለኛል፡፡*
>
> *እርግጥ፣ የሥዕል አስተማሪዎቻችን ራሳቸው ሥዕል የማይችሉ ነበሩ፡፡ አፋቸው ላይ የመጣላቸውን ነገር ሳሉ ማለት ነበር የሚቀናቸው፡፡ ለምሳሌ፤ መኪና፣ ሰው፣ እንስር፣ አበባ፡፡ በተለይ ሰባተኛ ክፍል ሆኜ በመስኮት ያዩትን ነገር፣ ለምሳሌ ባቡር ሲያልፍ ካዩ ባቡር ሳሉ፣ አህያም ካለፈች አህያ ሳሉ የሚሉ አስተማሪ እንደነበሩ ትዝ ይለኛል፡፡ በዚያን የልጅነት እድሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ችሎታ አላቸው ብለን ያመንባቸው መምህር ያጋጠሙን አራተኛ ክፍል ብቻ ነው፡፡ እሳቸውም እስከ ዛሬ ያልረሳኋትን ያችኑ "ጠረጴዛ" ዓመት ሙሉ ብላክ*

*ቦርድ ላይ ሲስሉልን ከርመው አዲሳባ ተቀየሩ፡፡ የሆነ ሆኖ የሰዓሊነቱን ሙያ ባልታደልም አድናቂነቱን አላጣሁምና አይቆጨኝም(1976፣37)፡፡*

ጸሐፊው በዚህ ወግ የግብር ይውጣ/ በግዴለሽነት የሚሰሩ ስራዎችን ተችተዋል፡፡ ትችቱ የቀረበበት መንገድ ግን ቀላልና አዝናኝ እንደሆነ መመልከት እንችላለን፡፡

በአጠቃላይ መደበኛም ሆኑ ኢ-መደበኛ ወጎች በውሱን ርዕሰ ጉዳይ ላይ ማተኮር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሚያተኩሩበት ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ አንበቢዎቻቸውን ያስተምራሉ ወይም ያዝናናሉ፡፡ ጸሐፊው ወጉን በሚሰልቅበት ወቅት እዛና እዚህ እየረገጠ የተለያዩ ሃሳቦችን የሚያሰፍርበት አጋጣሚ ቢኖርም ዋናውን ርዕሰ ጉዳይ ግን መለስ ቀለስ እያለ በማስታወስ ፍሬ ነገሩን ሳይስት ጽሑፉን ይጨርሳል፡፡

## *2. ልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፎች*

ልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፍ በእውናዊው አለም ያልተከሰቱ የፈጠራ ታሪኮችን በጣም ሳቢና አሳማኝ በሆነ መልኩ የመፍጠር ጥበብ ነው፡፡ የዚህን አለም ድብቅ ምስጢራት ከሰው ልጆች የህይወት መስተጋብር ጋር በማስተሳሰር ለመግለጽ ሲባል የሚፈጠር ጽሑፍ ነው፡፡

በጽሑፉ ውስጥ የሚካተተው መረጃ፡-

- *የደራሲው ምናባዊ ፈጠራ ነው፡፡*
- *የአፃፃፍ ስልት ምጥቀትና የትርጉም ጥልቀት ይታይበታል፡፡*
- *የትረካው አካሄድና የሴራው አወቃቀር ላይ ከፍተኛ ትኩረት ይደረጋል፡፡*
- *ካለንበት ጊዜና ቦታ አንስቶ ወደተለየ መቼት የማሻገር እንዲሁም በውስጡ ለያዛቸው ገጸባህሪያት ግድ እንዲኖረን የማድረግ አቅም አለው፡፡*

ስለሆነም ልቦለዳዊ የፈጠራ ስራ የተደራሲያኑን ትኩረት ስቦና ጠፍንጎ አስሮ የሚይዝ በጣም ሳቢና አስደሳች ስራ ነው፡፡ በዚህ ጎራ ከሚመደቡት የጽሑፍ አይነቶች መካከል ረጅም ልቦለድ፣ አጭር ልቦለድ፣ ግጥምና ተውኔት ይጠቀሳሉ፡፡

በመቀጠል እነዚህን አራት የልቦለዳዊ የፈጠራ ጽሑፍ ዘሮች በተናጠል እንመለከታቸዋለን፡፡

### ሀ. ስነግጥም

"ስነግጥም" የግጥም አፃፃፍ ጥበብ ማለት ነው፡፡ ይኸውም፡-

- *የግጥምን ቤት አመታት፣*
- *የስንኝ አመጣጠኑን፣*
- *ምቱንና ዜማውን፣*
- *የቃላት ምርጫውን፣*
- *የዘይቤ አጠቃቀሙን፣*
- *የሀሳብ አወራረዱን፣*
- *የምናብ ሀይሉንና*
- *የምስል ፈጠራ ሂደቱን በአጠቃላይ የግጥምን ምልዐተ ተፈጥሮ የሚያካትት ጥበብ ነው፡፡*

በሌላ አገላለጽ ግጥም፡-

- አንድን ሃሳብ ወይም ስሜት አጉልቶና አግዝፎ የሚያሳይ
- ይህንኑ ሀሳብ ወይም ስሜት አምቆ በተመረጡ ጥቂት ቃላት የሚያቀርብ
- ከነዚህ ውህደትም በሚሰርጸው ለዛው ስሜትን የመቆንጠጥና የማግለል ሀይል ያለው የፈጠራ ስራ የሚበጅበት ጥበብ ወይም ማበጃ መንገዱ ነው፡፡

በአንፃሩ ደግሞ "ግጥም" ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ ዘዴዎች በልዩ ሁኔታ በማዋሀድ የሚፈጠረውን ወይም በማበጃው አማካኝነት የሚበጀውን ጥበብ የሚያመለክት ቃል ነው፡፡

ግጥም ረዘም ያለ እድሜ ያለው የሰው ልጅ ሀብት ነው፡፡ ከጽሑፍ መፈጠር በፊት በቃል የነበረ እንደመሆኑም መጠን እድሜው የሰው ልጆች በቋንቋ መገልገል ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ ሊቆጠር ይችላል፡፡ እንደእድሜው አንጋፋነት በግጥም ላይ አስተያየት ከሰጡ የጽርእ ዘመን ሀያስያን ጀምሮ በየዘመናቱ እንደየዘመኑ የጽሑፍ ፍልስፍና፣ እንደየዘመኑ የህይወት ፈለግና እንደየሀያሲው አመለካከት የተለያዩ ብያኔዎች ተሰጥተውታል፡፡ ከውጪም ከሀገርውስጥም ያሉ የዘርፉ ምሁራን የግጥምን ምንነት አስመልክቶ የሰጧቸውን ብያኔዎች አለፍ አለፍ እያልን እንመለከታለን፡፡

ዝነኛው ገጣሚና ሀያሲ William Wordsworth ግጥምን በተመለከተ ሲገልጽ፡-

- *ምት ያለውና*
- *ምናባዊ የሆነ የብርቱ ስሜት መግለጫ ነው፤*
- *በለሆሳስ የተብላሉ የጠንካራ ስሜቶች ገንፍሎ መውጣት ነው ይላል፡፡*

Wordsworth ይህን አባባሉን ሲያብራራ ግጥም በተራው ጊዜ የታዘብናቸው ወይም ያስተዋልናቸው ድርጊቶችና ሁነቶችን በተረጋጋ መንፈስ ሆነን በምናብላላበት ጊዜ ለጉዳዩ ያለን ስሜት እየናረ እየናረ መጥቶ የመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደርስ ከውስጠኛው እኛነታችን በጽሑፍ መልክ እየገነፈለ የሚወጣው ሃሳብና ስሜት ግጥም ይሆናል ሲል ይናገራል(Preface to Lyrical Ballads) ፡፡

በሌላ ወገን ደግሞ Earlington Robinson ግጥም በሌላ መንገድ/አባባል ሊባል የሚያቅትን ጉዳይ ከሞላ ጎደል ስሜት ነኪ በሆነ ስልት የሚነግረን ቋንቋ ነው ሲል ይገልጸዋል፡፡ ስሜት በሁለቱም ብያኔ ሰጪዎች ዘንድ ትኩረት ያገኘ ጉዳይ በመሆኑ ግጥም ከስሜት ጋር ልዩ ቁርኝት ያለው ጥበብ መሆኑን መገመት እንችላለን፡፡

ወደሀገራችን ገጣሚያን ስንመጣ ሰለሞን ደሬሳ ለኔ ግጥም ማለት ይህ ነው ሲል የሚከተለውን ሃሳብ ልጅነት በተባለው የግጥም መድበሉ መግቢያ ላይ አስፍሯል፡፡

> *...የኑሮ አላማ እንደክብሪት ዋጋ ቁርጡ ባይገለጥልንም አላማ ለመኖሩ የፍጡሩ ከእለት ወደ እለት መፍቸርጨር በቂ ጠቋሚ ነው፡፡ የግጥም ፈንታ ይህን ግላዊ መፍጨርጨር... ከዚህ አለም ችላ ባይነት ጋር አያይዞ ማብላላት ይመስለኛል፡፡ ማብላላት፣ ማፋጨት፡፡ እያፋጩ ተቃራኒዎችን ማጣመድ፣ ተመሳሳዮችን ማለያየት፡፡ ከግጭታቸው ለአንድ አፍታ እንደበራሪ ኮከብ የሚታይ ግልፀ መፍትሔን ማዋለድ... (1963፣9)*

ፀጋዬ ገብረመድኅን በበኩሉ የግጥምን ምንነት ስርዓታዊነቱ ላይ በማተኮር እንዲህ ያብራራዋል፡፡

*በጠቅላላው የአሰካኩ ስርዓት እንደየምጣኔው ወይም እንደየስንኙ ቁጥር ልክ አይነተኛ ድንጋጌ ያደረገለትን ሃሳብ-ወለድ (ልብ-ወለድ) ስነ-ጽሑፍ ብቻ ሳይሆን፣ ግጥሙ ቤት የሚመታ ወይም የማይመታን እንቆቅልሽ ሆነ ምሳሌ ተረት፣ እንዲሁም፤ በቃለ-ውበቱና በቃለ-ኃይሉ፣ ወይም በድቀቱ ስምረት ለአእምሮ ለልቦናና ለስሜት የሚጥምን ባለስልትና ባለድንጋጌ የቋንቋ አደራደር ሁሉ ስነ-ግጥም (ፖኤትሪ) ይሉታል(1966፣7) ፡፡*

ከላይ የተሰጡትን ብያኔዎች ሰብሰብ በማድረግ ግጥም፡-

- *ምትና ዜማ ያለው፣*
- *በስንኞች የሚመጠን፣*
- *ቤት የሚመታ፣*
- *በዚህም ከስድ ጽሑፍ የሚለይ*
- *መልዕክትን (ሀሳብና ስሜትን) እምቅነትና ከረት ባለው መልክ ለመግለጽ የሚያስችል ስነጽሑፋዊ የስሜትና ሀሳብ ማቅረቢያ ነው ብሎ ጠቅለል ያለ ብያኔ መስጠት ይቻላል፡፡*

**የግጥም ባህሪያት፡-** በተለያ ምሁራን ዘንድ የሚጠቀሱ ግጥምን ከሌሎች የፈጠራ ጽሑፎች የሚመሳሰልም የሚለይም ቅርጽ የሚያደርጉት ባህሪያት የሚባሉት፡-

- *ተባጭ ነው*
- *ምናባዊ ነው፡፡*
- *ቁጥብነትና እምቅነት አለው፤*
- *ዜማዊ የሚሉት ናቸው፡፡*

**ተጨባጭነት**

ግጥም ተጨባጭ ነው ስንል ከያኒው በግል ህይወቱ ላይ ተመስርቶ ሃሳብና ስሜቱን በቋንቋ መሳሪያነት የሚያቀርበው ተጨባጭ በማድረግ ነው ማለታችን ነው፡፡ ገጣሚው በዚች አለም የህይወት ትውስብ ውስጥ ሲመላለስ የተበተበውንም ሆነ ሰርጥ ሰጥቶ ያሳለፈውን የኑሮ ዘሃ የታዘበውንም ሆነ ያደነቀውን የሰብዓዊ ባህሪ ገጽታ መነሻ አድርጎ አንዳች ጥበባዊ ቅርጽ በቋንቋ አማካኝነት ሲያቀርብ በገሃዱ አለም ሁላችንም የምናውቃቸውን ነገሮችና ግንኙነታቸውን እየገለጸ ነው፡፡ በዚህ አውድ ገጣሚው በህዋሳተ ስጋችን የምናውቃቸውንና በሱ ፈጠራ ውስጥ ደግሞ በህዋሳተ ልቦናችን የምናውቃቸውን ነገሮች ያቀናጀል፡፡ በዚህ ጊዜ በደራሲው ፈጠራ ውስጥ ያለው ነገር ተጨባጭ ሆኖ ይታየናል፡፡

**ምናባዊነት**

ሌላው የግጥም ባህሪ ምናባዊነት ነው፡፡ በአንድ በኩል ገጣሚው ምናባዊውን የአእምሮ ክፍል በውል በማሰራት የሚከይነው የፈጠራ ስራ መሆኑን ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል ከግጥ አንባቢው ወይም አድማጩ በግጥሙ የቀረበለትን ነገር የሚገነዘበው በአለመ ልቡናው መሆኑን ይጠቁማል፡፡ ግጥም ከተጨባጩ አለም የተወሰዱ ነገሮችን የሚይዝ ጥበብ ቢሆንም በከያኒውም ሆነ በአንባቢው/አድማጩ ዘንድ በጽሑፉ ውስጥ የሚሰፍረውን ሃሳብ በምናብ የመረዳት ሁኔታ ይታያል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ከዮሐንስ አድማሱ "ሞት በከተማ" ግጥም የተቀነጨቡ ስንኞች እንመልከት፡፡

*ከራስጌዬ ቆመ አያ ሞት መጣና፡፡*
*ቀና ብዬ አየሁት፣*
*እሱም አስተዋለኝ፣*
*እኔም አስተዋልሁት፡፡*
*አንዲት አደይ ይዟል-በግራ እጁ፣*

*በቀኝ እጁ ግና የወየበ ረብጣ፡፡*
*አለወትሮው ልብሱ፣*
*ቅርምዝ ይመስላል ይመስላል በለዴ*
*ገርጥቶ ወይቧል ደግሞ*
*መልኩ...*

በዚህ ግጥም ውስጥ ረቂቅ እሳቤ የሆነው ሞት ግዘፍ ነስቶ እንደሰው ሲለብስ ሲቆም፣ አይኖች ኖረውት ሲመለከት፣ በእጁም ቁሳቁስ ሲይዝ... እንመለከታን፡፡ ሞት የሚባል ፍጡር አይቶ የማያውቀው ገጣሚም ሆነ አንባቢ ይህን ሁሉ ድርጊት ሊረዳ የሚችለው በምናብ ርቆ በመጓዝና ትዕይንቱን ለመሳል በመሞከር ነው፡፡

**ቁጥብነትና እምቅነት**

ቁጥብነትና እምቅነት ትስስር ያላቸው ጽንሰ ሃሳቦች ሲሆኑ የግጥም አይነተኛ ባህሪው ናቸው፡፡ የግጥም ቁጥብነት ሀሳብና ቃላት መርጦ የመበጀቱ ምስጢር ማለት ነው፡፡ ግጥም ጽዩፍ ነው፤ ለጉዳዩ ቅርበት የሌላቸውን ትርኪምርኪ ቃላት የማግበስበሻ ከርስ የለውም፡፡ ሃሳብን በዝርዝር ከማቅረብ ይልቅ ስኬታማ ቃላትን በመምረት ፍንጭ ሰጪና አንኳር የሆኑትን የአንድ ተያያዥ ሃሳብ ክፍሎች መርጦ በጥቆማ መልክ ያቀርባል፡፡ በዚህም የተነሳ በግጥሙ በተነገረው ጉዳይ ጠቋሚነት ያልተነገረውን እየፈለጉ መሙላት የአንባቢው/አድማጩ ድርሻ ነው፡፡ እነዚያ የተመረጡ ስኬታማ ቃላትና አንኳር ጉዳዮች ብዙ ሊሉና ብዙ ሊጠቁሙ የሚችሉ በመሆናቸው ግጥም ሰፊ ሃሳብ አምቆ የመያዝ ሀይል አለው እንላለን፡፡

በታገል ሰይፉ ቀሮውን አትንኩት የግጥም መድበል ላይ ከተካተቱት ግጥሞች መካከል “ወረት” የግጥምን የእምቅነትና ቁጥብነት ባህሪ ለማስረዳት ጥሩ ምሳሌ ይሆናል፡፡

*“ነይ! ነይ! ነይ! ነይ!”*
*አነቃት*
*“ሂጂ! ነይ! ሂጂ! ነይ!”*
*ነቀነቃት፡፡*
*“ሂጂ! ሂጂ! ሂጂ! ሂጂ!”*
*ለቀቃት፡፡*

እንደምንመለከተው ይህ ግጥም አምስት ቃላትን ብቻ በመሰካካት የተፃፈ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በወረት በያንዳንዱ ደረጃ ላይ ሰዎች የሚያሳዩትን ባህሪና የሚፈጽሙትን ድርጊት በሚገባ ያሳያል፡፡ የወረት ፍቅር የጀመሩ ሰዎች በፍቅራቸው የመጀመሪያ ሰሞን አንድነታቸው ያይላል፣ የሚለያዩም አይመስሉም፡፡ እየቆየ ጊዜያዊ ስሜታቸው እየሸሻቸው ሲመጣ ግንኙነታቸው ያዝ ለቀቅ ይሆናል፣ ፍቅራቸው ተሟጦ ያለቀ እለት ደግሞ አይነህ ላፈር፣ አይንሽ ላፈር ተባብለው መለያየታቸው አይቀሬ ነው፡፡ እንግዲህ ይህን ሁሉ ሃሳብ ነው ታገል ሰይፉ በጥንቃቄ በተመረጡ ስኬታማ አምስት ቃላት ውስጥ አምቆ ያቀረበልን፡፡

**ዜማዊ**

ግጥም በተፈጥሮው ለመደመጥ የሚበጅ የፈጠራ ስራ በመሆኑ ዜማዊ ነው፡፡ ዜማዊነቱ የሚፈጠረው ከምቱ ነው፡፡ የምቱ ስልትና ስርዓታዊነት እንዲሁም የአንዳንድ ቃላት የተለየ ባህሪ ከሌሎች ቃላት ጋር በሚሰለፉበት ወቅት አደራደራቸው የሚያመጣው ቃና ግጥሙን ሙዚቃዊ ሊያደርገው ይችላል፡፡ የሚፈጠረው ዜማ በአድማጩ ውስጥ አንዳች የደስታ፣ የሀዘን፣ የሰቀቀን፣...ስሜትን ያጭራል፡፡

ከላይ የቀረቡት ባህሪያት የግጥም አይነተኛ መገለጫዎቹ ናቸው፡፡ በመቀጠል ግጥም ለመፃፍ በምንሞክርበት ጊዜ መነሻ ሊሆኑን የሚችሉ ስልቶች/ዘዴዎችን እንመለከታለን፡፡

**ግጥምን ግጥም የሚያሰኙ ነገሮች**

**መቼት**

ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው ግጥም ከስሜት ጋር ልዩ ቁርኝት ያለው ጥበብ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በውስጣችን ድንቅ ስሜት ትተው የማለፍ ሀይል ያላቸው ስፍራዎችን ወይም ክስተቶችን እናይና ግጥማችንን ይህ ቦታ ወይም ክስተት በፈጠረብን ስሜት ዙሪያ መገንባት እንፈልግ ይሆናል፡፡ ስለዚህ መቼት በግጥም መፃፍ ሂደት ውስጥ ትኩረት የሚሰጠውና አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ መቼቱ ውብ የአትክልት ስፍራ፣ ጦር ሜዳ፣ የተዋከበ ገበያ፣ ታሪካዊ ስፍራ በአጠቃላይ አካባቢያዊ ወይም ማህበራዊ መቼት ሊሆን ይችላል፡፡ በግጥማችን የምንገልፀው ስሜት ከሰው ገጠመኝ ጋር የሚገጥምና የሚታመን ይሆን ዘንድ የሆነ ስፍራና ጊዜ ላይ መቀመጥ ይገባዋል፡፡

በግጥም ውስጥ የሚያጋጥመን መቼት እንደመንግስቱ ለማ "በጠራ ጨረቃ" ግጥም ውስን ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን የስሜት ሁኔታን ብቻ ሊያንፀባርቅ ይችላል ምድራዊ ያልሆኑ ገጠመኞች ሊካተቱ ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ መቼት አንባቢው በግጥም የሚገለጸውን ሀሳብና ስሜት በምናቡ ለመቅረጽ ይችል ዘንድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

ስለግጥም መቼት ይህን ያህል ካልን በመቀጠል በምን አይነት መልኩ ግጥማችን ለያዘው ሀሳብ ተስማሚ የሆነ መቼት መፍጠር እንደምንችል አንዳንድ ሀሳቦችን እንመለከታለን፡፡

ግጥም ለመፃፍ ስንነሳ ማሳካት የፈለግነውን አላማ ወይም ማግኘት የፈለግነውን እርካታ ከዳር ለማድረስ ግጥማችንን በምናባዊ አለያም አካባቢያዊና ማህበራዊ መቼት ላይ መመስረት እንችላለን፡፡ ዋናው ቁም ነገር አላማው ነው፣ ማለት/ መተንፈስ የፈለግነው ጉዳይ ምንድን ነው? ስለአንድ ታሪካዊ ጉዳይ መፃፍ ከሆነ ከጊዜው ጋር የሚሄድ አካባቢያዊና ማህበራዊ መቼት መቅረፃችንን ማረጋገጥ አለብን፡፡ በዚህ አጋጣሚ ስለቦታና ጊዜው ያለን መረጃ ትክክለኛ መሆን አለበት ይህ ካልሆነ ግን ተአማኒነት የሌለው ምስል በግጥማችን እንቀርፃለን፡፡ ለገጣሚ ግን ታሪክ ላይ ከማተኮር ይልቅ የተሻለው የመፃፍ ፍላጎት ባደረበት ጊዜ የሚሰማውን ነገር በተሰማው መንገድ ማቅረቡ ነው፤ የስሜት ሀይልና ትኩሳት እንዲኖር፡፡

መቼታችን ከታዘብናቸው ሁነቶችና አካባቢዎች ተነስተን ብንቀርፀው መልካም ነው፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ስለምናውቀው ነገር ስንጽፍ የተሻለ እንጽፋለን፡፡ እንደፈጠራ ጽሑፍ ፀሐፊም የተለያዩ አካባቢዎችን ማስተዋሉ ጠቀሜታ አለው፡፡ ሁልጊዜም የሚያስደንቀን ስፍራ ስናይ ያንን ስፍራ በምን አይነት መልኩ ለፈጠራ ስራ ማዋል እንደምንችል ማውጠንጠን መቻል አለብን፡፡ ስለዚህ ወደየትኛውም አካባቢ ስንሄድ በልዩ ሁኔታ መመልከትን መልመድ አለብን፡፡ እስከዛሬ ያላስተዋልናቸው ጥቃቅንና የተለመዱ ጉዳዮች ላይ በማተኮር፤ የአበቦች ድምቀት፣ የነፋስ ሹክሹክታ፣ የፀሐይ ሙቀት፣ የወፎች ጫጫታ፣ የሰዎች ንግግር፣…ከስከዛሬው ጎልቶና ደምቆ ሊታየንና ሊሰማን ይገባል፡፡

መቼት ተምሳሌታዊ ሊሆን ይችላል- አስደሳች ወቅትን፣ መሪር ሁኔታን፣ ትዝታን፣ ህልምን … የሚገልጽ፡፡ ለምሳሌ አካባቢያዊ መቼቱ ብሩህ ሰማይ፣ ደማቅ የፀሐይ ብርሃን፣ ለምለም መስክ… የሆነ ግጥም ከአካባቢያዊ መቼትነቱ በተጨማሪ ደስታን፣ ተስፋን ሊያሳይ ይችላል፡፡

**ድምፀት**

ከላይ እንደተመለከትነው መቼት የግጥሙ ድምፀት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ስለሆነም ተፈላጊውን ድምፀት ለማምጣት መቼት አቀራረፃችንን ማስተካከል አለብን ማለት ነው፡፡ ድምፀት በአንድ ግጥም ውስጥ ለሚቀርብ ርዕሰ ጉዳይ ተናጋሪው ሰብዕና የሚኖረው ስሜትና አመለካከት መግለጫ የሆነ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ድምፀት የተለየ ምጣኔ ያለው የድምጽ መውደቅ መነሳት የድምጽ መለዋወጥ ሊፈጥረው ይችላል፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን የተናጋሪው አመለካከት መግለጫ ነው፡፡ ይህ አመለካከት የሀዘን፣ የምሬት፣ የንዴት ፣ የደስታ፣ የአድናቆት፣ የምፀት፣ የማሾፍ፣ የጥሞና፣ የማቅረብ፣ የማራቅ… ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገሩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ቀጥሎ የቀረበውን የደበበ ሰይፉ ግጥም እንመልከት፡፡ የግጥሙ ድምጸት ተስፋ መቁረጥን እንድናስብ የሚያደርገን አይነት ነው፡፡

***ራሴን በላሁት***
*ገብቼ ሱባዔ*
*ከብቻ ጉባዔ፣*
*ላያሌ ዓመታት*
*በእኔነት ማሳ ተመላልሼበት፣*
*ወጥቼ ወርጄበት፣*
*አዝመራ ባጣበት፣*
*ራሴን በላሁት*
*እየመነዘርሁት፡፡*
*እያመናዘርሁት፡፡ (ለራስ የተፃፈ ደብዳቤ 1992፣32)*

**ምሰላ**

ገጣሚ ግጥሙን የሚጽፈው ስሜቱንም ለሌሎች ለማስረዳት የሚጥረው ምስል በመፍጠር ነው፡፡ የሚፈጥራቸው ምስሎች፣ የሚፈጥራቸው ዘይቤዎች፣ የሚመርጣቸው ቃላት እኒህንም አሰናኝቶ የሚፈጥራቸው ስንኞች ያላቸው ዝንባሌ የሚጽፍበትን ሀሳብ ምንነት ያሳብቃል፡፡ ጥሩ የሚባል ግጥም የሚደመጥ የሚሰማ ስዕል ነው፡፡ ይህን ስዕል የሚያሳየን ምናባዊ ምስል በመፍጠር ነው፡፡ ገጣሚው ሊያሳየን የፈለገውን አለም የሚያስተናግደው በህዋሳተ ልቦናችን የምናሽታቸው፣ የምንቀምሳቸው፣ የምንዳስሳቸው፣ የምናያቸው፣ የምንሰማቸው ነገሮችን በመፍጠር ነው፡፡

በተደራሲው አቅራቢያ የማይገኙ ነገሮችን ሁሉ አግዝፎ ለማሳየት የሚገለገለው ምስያን ነው፡፡ ስለዚህ በተለያየ መንገድ በአመቺው ስነግጥማዊ ብልሃት ተፈጥረው በግጥም ውስጥ የሚቀርቡና ተደራሲው በአንዱ ወይም በከፊሉ ወይም በሙሉ ህዋሳተ ልቦና የሚጋራቸው ነገሮች ምስል /Image/ ይባላሉ፡፡

እነዚህ በአለመ ልቡናችን የሚፈጠሩ የምናብ ምስሎችና የሚፈጥሯቸው ልዩ ልዩ ስሜቶች የሚበጁበት የቋንቋ አጠቃቀም ብልሃት ወይም ጥበብ ደግሞ ምሰላ /Imagery/ ይባላል፡፡ "… ምሰላ ገጣሚው ገጠመኙንና እውነቱን ወደ አንባቢ ልቡና የሚያቀርብበት፣ አንባቢም ምስሎችን መልሶ በማዋቀር ንቁ የምናብ ተሳታፊ የሚሆንበት አጋጣሚ ስለሚፈጥር የስነጽሑፋዊ ተግባቦት አንድ አቢይ ማኼጃ ነው፡፡" (ብርሃኑ 1999፣300) ስለዚህ ገጣሚው ለህዋሳተ ስጋችን ሩቅ የሆኑ ነገሮችን አቅርቦና አግዝፎ ለማቅረብ ምሰላን ይጠቀማል፡፡ የምስል ፈጠራ ሂደቱ ከገጣሚ ገጣሚ ሊለያይ ይችላል፡፡ የሚከተለው በሚታዩ ምስሎች የተሞላ የሰለሞን ደሬሳ ግጥም በምሳሌነት እንመልከት፡፡

**በሃምለት አገር**

*ከተራራ ላይ ቅርብ ባህር ሲያዩ*
*የተሰነጠቀ መስሎ፣ ለሁለት ሰማዩ*
*በሰንጥቁ መሬት ሲገባ*
*ጥቁር ቅጠላዊ የህልም ገለባ*
*ደረቅ አረንጓዴ አንጀት የሚያባባ፣*
*ሰወርድ ቁልቁለቱን*
*ሰሄድ? ሰንከባለል?*
*አገጩ ስር ጥቁር ባህር*
*ባሏጋ ልወረወር*
*ልሰምጥ፣ ልንሳፈፍ፣ ወይንስ ልሳፈር*
*ወደ ሌላ በሌላ በር፡፡ (ልጅነት 1963፣16)*

**ጭብጥ**

እንደልቦለድ ሁሉ በግጥም ውስጥ ጭብጥ የሚባለው ገጣሚው ሊያስተላልፍ የፈለገው፣ በተገለጠው ስሜት አማካኝነት የተላለፈው መልዕክት ነው፡፡ የግጥማችንን ጭብጥ ከአንድ ጽንሰ ሀሳብ፣ አስደናቂ ክስተት፣ ታሪክ፣ ስሜት፣ ሰው፣ ገጠመኝ ልንመዘው እንችላለን፡፡

**ምት**

በስነግጥም ምት የሚባለው እንደልብ ትርታ በገሃዱ አለም እየተፈራረቁ በድግግሞሽ እንደሚኖሩ ሌሎች ተፈጥሯዊ ነገሮች ሁሉ ተደጋግመው በሚመጡ ሀረጎች መሃል ያለውን የተወሰነ የጊዜ መጠን መጠበቂያ ስልት ነው፡፡ ምት በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ ድግግሞሽ አለ፡፡ ማንኛውም ዜማ የሚመነጨው ከድግግሞሽ ነው፡፡ ግጥም በባህሪው ዜማዊ እንደመሆኑ መጠን የተመጠኑ የምልዐት ማስገኛ ክፍሎቹ ከሚኖራቸው ድግግሞሽ ሙዚቃዊ ቀና ይመነጫል፡፡

**የቃላት ምርጫ**

የግጥም ቋንቋ በሁለት ምክንያቶች የተነሳ የተለየ ቋንቋ ነው፡፡ የመጀመሪያው አፈንጋጭነቱ ሲሆን ይህም ለቋንቋው ሰዋሰዋዊ ስርዓት ካለመገዛቱ ጋር ይያያዛል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለዛ ያለው መሆኑ ነው፡፡ የውጫዊና ውስጣዊ ሀይሉ ስሙር ስሜት በአንድነት ሆኖ የሚፈጥረው አንዳች ንቃት ነው፡፡ ማራኪነት አርኪነት እንዲያገኝ የግጥም ቋንቋ አንዳች የውበት ሸማ ሊጎናጸፍ ይገባዋል፡፡ ለዛ አንድ ግዙፍ ቢሉ ረቂቅ ነገር ከተሰራባቸው ምልዓት ማስገኛ አካላት ቅንብር የሚሰርጽ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ የአንድ ነገር ለዛ

የሚታወቀው ደረጃውም የሚገኘው የነገሩ ምልዓት ማስገኛ ቅንብር ለተመልካቹ/ ለሰሚው/ ለአንባቢው ስሜት በሚኖረው ቅርበት ነው፡፡ የአንድ ነገር ለዛ ከሰው ወደ ሰው ይለያይ እንጂ ለዛ ሳቢነት፣ ማራኪነት፣ ለስሜት ቅርብ መሆን ነው፡፡ በሌላ አባባል ለዛ የአድማጩን/ የአንባቢውን ስሜትና ሀሳብ አስተባብሮ በማይጋፉት አንዳች ሞገስ ተቆጣጥሮ ባገላለፁ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ስኬታማ የማድረጊያ ሀይል ነው፡፡ የግጥም ቋንቋ ለዛ ዋነኛ ምንጭ ደግሞ ዘይቤና የተመረጡ ቃላት ናቸው፡፡

ጥሩ ገጣሚ ከቃላት ጋር መጫወትን ማዘውተር አለበት፡፡ ገጣሚያን ግጥማቸውን ለመፃፍ የተለያዩ ቃላትን ሲመርጡ ለፍካሬያዊ ፍቹ የተለየ ትኩረት መስጠት አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ብዙ ነገሮችን አምቆ የመያዝ ችሎታ ስላለው ነው፡፡ አንባቢውም ቢሆን በፍካሬያዊ ፍቺ ላይ ማተኮር አለበት፡፡ እያንዳንዱ ገጣሚ የራሱ የሆነ የቃላት ምርጫ አለው፡፡ እንዲያውም የገጣሚ ስልት ከሚታወቅባቸው መንገዶች አንዱ የቃላት ምርጫ ነው፡፡ የቃላት ምርጫ የሚለያየው በገጣሚያኑ የገጠመኝ ልዩነት የምናብ አቅም… ወዘተ ነው፡፡ ገጣሚያን እንደየምርጫቸው ትኩረት ሊሰጧቸው የሚችሉ፣ ምናልባትም አዘውትረው ስለሚገለገሉባቸው የአፃፃፍ ስልታቸው መገለጫዎችም የሚሆኑና ለግጥም መፃፊያ በልዩ ልዩ መንገድ የሚረዱ የቃላት አይነቶች አሉ፡፡

ገጣሚ ግጥሙን የሚጽፈው በህይወት ገጠመኙ ላይ ተመርኩዞ ነው፡፡ በግጥሙ ውስጥ የሚያሰፍረውን/የሚገልፀውን ስሜት በቋንቋው ውስጥ ያሉ ቃላትን በመምረጥና በልዩ ሁኔታ በማቀናበር ይገልፃል፡፡ ይህ ገለጻና የገጣሚው ገጠመኝ በፈጠራ አማካኝነት ሲዋሀዱ ገጣሚው ምርጥ ግጥም ፃፈ እንላለን፡፡ ነገር ግን በገጠመኙና በአገላለጹ መካከል ውህደት ከሌለ ግጥሙ አንባቢን የመሳብ ሀይሉ ደካማ ይሆናል ማለት የተፈለገውም ጉዳይ በተሳካ ሁኔታ ላይተላለፍ ይችላል፡፡

ግጥም ከገጠመኞቻችን ያተረፍናቸው ስሜቶች ገለፃ እንደመሆኑ መጠን ገጠመኙና ገጠመኙ የሚገለጽበት መንገድ ሊነጣጠሉ አይችሉም፡፡ ለአቀራረቡ ወይም አገላለፁ ትኩረት ያልሰጠበት ግጥም ግጥም መሆኑ ይቀርና የሀሳቦችና የስሜቶች ስብስብ ብቻ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ግጥምን ግጥም የሚያሰኘው የሚባለው ነገርና የተባለበት መንገድ በአንድነት ሲዋሀዱ ነው፡፡

**የግጥም አፃፃፍ ሂደት**

በዚህ ርዕስ ስር የሚቀርቡት የመንደርደሪያ ሀሳቦች በግጥም አፃፃፍ ሂደት ውስጥ ሊረዱን ይችላሉ፤ ነገር ግን ስለነዚህ ጉዳዮች እየተጨነቅን የፈጠራ ሂደቱን ማስተጓጎል አይገባም፡፡ ለአንዱ ገጣሚ የተመቸው መንገድ ለሌላው ላይመቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም የራሱን መንገድ ይፈልጋል፡፡ ይህ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ክፍል አንድ ገጣሚ የግጥም መነሻ የሚሆን ሀሳብ በአእምሮው ውስጥ ከተፀነሰበት ቅፅበት ጀምሮ ግጥሙን በጽሑፍ እስኪያሰፍረው ድረስ የሚያልፍበትን የማብላላትና የመፃፍ ሂደት ለማየት እንሞክራለን፡፡

የልቦለድ ደራሲያንና ጸሐፌ ተውኔቶች በአብዛኛው የፈጠራ ስራቸውን የሚጀምሩት አጽመ ታሪክ በማዘጋጀት ወይም ትልም በመንደፍ ነው፡፡ ገጣሚ ግን አንዳች የተዋቀረ ሴራ ያለው ታሪክ ስለማይጽፍ በአብዛኛው ይህን ማድረግ አይጠበቅበትም፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው "ግጥም በለሆሳስ የተብላሉ ጠንካራ ስሜቶች ገንፍሎ መውጣት" መሆኑን William Wordsworth ተናግሯል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ገጣሚው የፈጠራ ስራውን የሚሰራው ሀሳቡንና ስሜቱን በምናቡ በሚያመላልስበት ወቅት ነው ማለት ነው፡፡ የሚሰማውንና የሚያስበውን በቀጥታ ወረቀት ላይ ያሰፍራል፡፡

የምናብ ሀይል የፈጠራ ስራ መሰረት ነው፡፡ ግጥሙ የሚመጣው ከገጣሚው ምናብ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የፈጠራ ሂደቱ የሚጀምረው ገጣሚው እንደገጣሚ መፃፍ ከመጀመሩ በፊት በአእምሮው ውስጥ ብልጭ ከሚለው መነሻ ሀሳብ መፀነስ ጀምሮ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ገጣሚው በአእምሮው የተፀነሰውን ሀሳብ ስኬታማ ባልሆነ መንገድ በጽሑፍ ሊያሰፍር ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ እንደገና መሞከር ይጠበቅበታል፡፡ በአብዛኛው ግን የመጀመሪያው ንድፍ ቅርፁን ለማሳመር እዚህና እዚያ ጥቂት የመቀባባትና የማሳመር ስራ ተሰርቶበት ወደ ዋናው ግጥምነት ይዳብራል፡፡ በመጀመሪያው የግጥም ሀሳብ ላይ እኛን የሚያረካን ደረጃ ላይ እስኪደርስ ድረስ ደግመን ደጋግመን የማስተካከል ስራ በመስራት ትክክለኛውን ስሜት ለዛ ባለው መልኩ ማስፈር ይቻላል፡፡

በአእምሯችን ሀሳብ ተፀንሶ የመፃፍ ስሜት በተሰማን ቅጽበት ሀሳባችንን በጽሑፍ የማስፈር ልማድ ሊኖረን ይገባል፡፡ በሌላ ስራ ተጠምደን እንኳ ቢሆን ስራውን አቋርጠን መፃፍ አለብን እንጂ ያንን ቅጽበት ማሳለፍ የለብንም፡፡ ምክንያቱም ስራችንን ተመልሰን ልንሰራው ብንችልም ያንን የፈጠራ ስሜት ግን መልሰን ለማምጣት እጅግ አስቸጋሪ ይሆናልና ነው፡፡ የጀመርነውን አንድ ግጥም እስክንፈፅመው ድረስ በፍፁም ፀጥታና ደስታ ውስጥ ሆነን ግጥሙ ከነፍሳችን እንዲፈስ መፍቀድ አለብን፡፡ የመፃፍ ስሜቱ ከሌለን ግን አእምሯችንን በማስጨነቅ ለመፃፍ መሞከር የለብንም፡፡

ሁልጊዜ አንድ ግጥም መፃፍ ከጀመርን ትኩረታችንን እሱ ላይ ብቻ ማድረግ አለብን፡፡ ስለሌሎች መፃፍ ስለምንፈልጋቸው ግጥሞች ማሰብ የለብንም፡፡ ሀሳባችን ሁሉ አሁን እየፃፍነው ባለው ግጥም ላይ ማረፍ አለበት፡፡ ስለምንጽፈው ግጥም ማሰብ ማለት ግን ምን ልፃፍ እያሉ መጨነቅ ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም በአእምሯችን ውስጥ የተፀነሰውን ሀሳብ በምን አይነት መልኩ ላስቀምጠው ብሎ ማሰብ ነው፡፡ ብዙ ግጥሞች የሚፃፉት በአንድ ጊዜ ቁጭታ ነው፤ ምክንያቱም አንድ ጊዜ ሀሳቡ በአእምሯችን ውስጥ ተብላልቶ የራሱ የሆነ ቅርጽ ከያዘ በኋላ ግጥሙ በቀላሉ እየገነፈለ ስለሚፈስ ነው፡፡ አንድ ጊዜ መፍሰስ ከጀመረ በኋላ ግን ግጥሙ በሚመራን መንገድ ተከትለን መጓዝ ነው፡፡ አንዳንድ ገጣሚያን የፃፏቸው ግጥሞች በያዙት ቅርጽ ሆነው አእምሯቸው ውስጥ እንደተከሰቱ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ከኛ የሚጠበቀው ወረቀትና እስክሪፕቶ ይዘን ከውስጣችን የሚገፋንን ስሜት ማድመጥ ነው፡፡

ስሜት በአንድ ሰው ውስጥ ያለ የደስታ፣ የፍቅር፣ የህመም፣ የቁጣ፣ የሰቀቀን፣ የሀዘን፣ ስሜት ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ስሜቶች የአንድ ሰው አእምሮ የሚገኝበት ሁኔታ ነፀብራቆች ናቸው፤ ወይም በውስጡ

የሚመላለሰው ሀሳብ ውጤቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ስሜት በአእምሯችን ውስጥ የሚፈጠር ጠንካራ ሀሳብ በድርጊታችን (ማልቀስ፣ መቆጣት፣ በደስታ መፈንደቅ...) በኩል መገለጥ ነው፡፡

የገጣሚ ስሜት በቃላት አማካኝነት ወረቀት ላይ ይገለጣል፡፡ በጥሩ ሁኔታ የተገለጠ የስቃይ ስሜት አንባቢውን በእንባ ሊያጥብ ይችላል ወይም በደስታ ስሜት ሊያስፈግግ ይችላል፡፡ ይህ ማለት ገጣሚው የተሰማውና ወረቀቱ ላይ ያሰፈረው ስሜት ወደ አንባቢውም ተጋብቷል ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው መፍጠር የሚችለው ፍፁም ውስጣዊ ሰላም ባገኘበት ወቅት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በተረበሸ አካባቢ ሆነን ልንጽፍ እንችላለን፡፡ ለመፃፍ ግን ፍፁም ሰላምና ፀጥታ የሰፈነበት ስፍራ ተመራጭ መሆኑን ብዙዎች ይስማሙበታል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ በገበያ ቦታ ወይም በሌላ ጫጫታ በሚበዛበት አካባቢ የተፃፉ በርካታ ግጥሞችን ልናገኝ እንችላለን፡፡ ዋናው ቁምነገር በምዕራፍ ሁለት ትምህርት እንደተጠቀሰው ለፈጠራ ስራ የሚስማማንን ቦታና ሁኔታ ለይተን ማወቅ ነው፡፡

እንደጀማሪ ገጣሚ በህይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ነገሮች ትኩረት ሰጥተን ልናስተውላቸው ይገባል፡፡ “ምድሪቱ በሰዎችና በሌሎች ስፍር ቁጥር የሌላቸው ፍጡራን የተሞላች ነች፡፡ ሁሉም ለመታየት ታይተውም ለመገለጥ የኛን ማስተዋል ይፈልጋሉ፡፡” (Spiegelman: 2005,11) ከያንዳንዱ ሁኔታ አንድ አዲስ ነገር ለመማር ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል፡፡ በየአንዳንዱ የስሜት ህዋሳችን በኩል እንማራለን በመሆኑም እያንዳንዱን የአስተውሎታችንን ውጤት በአእምሮ መዝግቦ ማኖር ያስፈልጋል፡፡ እንዲህም በማድረጋችን ያስተዋልነውን ነገር በአዲስ መንገድ የማየትና የመረዳት እድል ይኖረናል፡፡

ፍርሃት፣ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ ማጣት፣ ረሀብ፣ ድህነት፣ ህመም፣ ድል፣ ሽንፈት፣ ስኬት፣ ውድቀት፣... በህይወታችን ውስጥ ከሚያጥሙን ክስተቶች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ገጠመኝ ላይ መፃፍ አይጠበቅብንም ይልቁንም ስሜታችንን ዘልቀው መንካት የቻሉትን ብቻ ለግጥም እንመርጣቸዋለን፡፡ እነዚህ ክስተቶች/ገጠመኞች ልዩ በመሆናቸው ለሌሎች ልናጋራቸው የምንፈልጋቸው አይነት መሆን አለባቸው፡፡ ስለዚህ የትኞቹ ገጠመኞች ለዚህ ጉዳይ መታጨት አለባቸው የሚለውን መወሰን መቻል አለብን፡፡ ከሌሎቹ ገጠመኞች የበለጠ ስሜት የሚፈጥርብንና በኛ አይን ትልቅ ርዕሰ ጉዳይ መስሎ የሚታየን ነገር ላይ ብንጽፍ ይመረጣል፡፡ አንዳንድ ጊዜ አዲስ ነገር ባያገጥመንም የተለመዱ ጉዳዮችን በተለየ መንገድ በማስተዋል ስሜታችን ሊነካና ልንጽፍ እንችላለን፡፡

ግጥም ስንጽፍ በመጀመሪያ ከውስጣችን ገንፍሎ የወጣውን ስሜት በቀጥታ እናሰፍራለን፡፡ ይህ ከውስጣችን እንድንፈጥር ወይም ስሜታችንን እንድንገልጽ የሚገፋፋን ሀይል ውጤት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ገጣሚው ስለለአፃፃፍ ህግና ደንብ ሳይጨነቅ ከውስጡ እየገነፈለ የሚወጣውን ሀሳብና ስሜት በቀጥታ ያሰፍራል፡፡ ግንፍልታው ካለፈና የመጀመሪያው ንድፍ ከሰፈረ በኋላ ግን የሰፈረውን ሀሳብ በእርጋታ ማስተዋል ይከተላል፡፡ በዚህ ደረጃ ላይ ግጥሙን የማሻሻልና ምርጥ በሆነ መንገድ የማበጀት ስራ ይሰራል፡፡ የተመኘውን አይነት ምትና ዜማ እስኪያመጣለት ድረስገጣሚው መልሶ መላልሶ ግጥሙን ያደራጃል፡፡ በግጥሙ ውስጥ የተጠቀማቸውን ቃላት፣ ዘይቤ፣ መቼት ፣ ድምፀትና ምስላ ተገቢነት ያረጋግጣል፡፡ ትክክለኛውን ቅርጽ ለማምጣት ግጥሙን በስንኝና አርኬ ያደራጃል፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ

ደግሞ ደጋግሞ እያነበበ ያስተካክላል፣ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት በትክክል ማስተላለፉን ያረጋግጣል፡፡ ክለሳውን በሚጨርስበት ወቅት ግጥሙ የመጨረሻ ቅርፁን ይይዛል፡፡

**ለ. አጭር ልቦለድ**

አጭር ልቦለድን ከሚይዘው ገጸባህሪያት ብዛት፣ ታሪኩ ከሚቀርብበት ቃላት ውሱንነት፣ ከሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ ነጠላነት በአጠቃላይ በጣም የተቆጠበ የስነጽሑፍ ዘር ከመሆኑ አኳያ የተለያዩ ብያኔዎች ተሰጥተውታል፡፡ ከነዚህ መካከል አልበርት እና ጄሲ አጭር ልቦለድ በዝርው የተፃፈ፣ ጥብቅ በሆነ ቁርኝት የተዋቀረ፣ አብዛኛውን ጊዜ ከአስር ሺ ቃላት የማይበልጥና የፈጠራ ጽሑፍ ባህሪያትን የተላበሰ ስራ ነው ሲሉ ይበይኑታል፡፡ (1968፣ xv-xvi) አጭር ልቦለድ እንዴት ይፃፋል የሚለውን ከማየታችን በፊት በዚህ ብያኔ መሰረትነት ላይ ጥቂት ስለባህሪያቱ እንመለከታለን፡፡

አጭር ልቦለድ በጣም የተመጠነ ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ጊዜ ቆይታ ወይም ሳናቋርጥ አንብበን የምንጨርሰው አይነት የፈጠራ ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ጥድፊያ፣ ነጠላ ውጤትና ቁጥብነት የአጭር ልቦለድ ባህሪያት ሊሆኑ ችለዋል፡፡ የአጭር ልቦለድ መንገድ አጭርና ቀጥተኛ ነው፡፡ ከመንገዱ መጨረሻ ከተደረሰም በኋላ ሌላ መንገድ አይኖረውም፤ በሌላ አነጋገር ግቡ እዚህ ላይ ያበቃል ማለት ነው፡፡

ማንኛውም አጭር ልቦለድ አንድ ነጠላ ግብ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህም ግብ ከተደረሰበት በኋላ ታሪኩ ሊቀጥል አይችልም፡፡

> *በዚህ መርህ መሰረት የድርሰቱ አጀማመር፣ የገጸባህርያቱም ሆነ የሚንቀሳቀሱበት መቼት እውቂያ፣ ወደ ዋናው ታሪክ የሚደረገው ጉዞ፣ የታሪኩ አከርካሪ የሆነው ግጭት፣ የገጸባህርያት ገለጻም ሆነ ምልልስ ዘርፋዘርፍ ነገር ሳይጨምሩ በውል ተሰናስለው ወደተባለው ውጤት ማምራት ይኖርባቸዋል፡፡ ከመጀመሪያው አረፍተ ነገር ጀምሮ የሚባለው ነገር ሁሉ ለሱው አንዳች ድርሻ የሚያበረክት እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ (የስነጽሑፍ መሰረታውያን 1998፣229)፡፡*

ጥድፊያ የሚያስፈልገው ወደ ግቡ ለመድረስ ነው፡፡ ይህንን ፍጥነት የሚያስቀስሱ ነገሮች አሉ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ፍጥነትን የሚያስቀስስ ነገር የሰው ብዛት ነው፡፡ ሰው ሲበዛ ግርግር ይፈጠራል፡፡ የዋና ገጸባህሪያቱን ቁጥር ማሳነስ የታሪኩን ፍጥነት መጨመሪያ አንዱ ዘዴ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በአጭር ልቦለድ ውስጥ ከሁለት በላይ ዋና ገጸባህሪያት ባይኖሩ ይመከራል፡፡

ጥድፊያን የሚያጓትት ሌላው ነገር የገለፃ ዘዴ ነው፡፡ ደራሲው የሚገልፃቸው የገፀባህሪያትና የመቼት ሁኔታዎች በተቻለ መጠን የታሪኩን ፍጥነት የማይገቱ መሆን አለባቸው፡፡ የተንዛዛ ገለፃ ታሪኩን ያንጓትተዋል፡፡

ከቁጥብነት አንፃር አጭር ልቦለድ በተቻለ መጠን ሰብሰብ ማለት አለበት፡፡ ስለዚህ በታሪኩ ውስጥ የሚደረጉ ገለፃዎች የተቆጠቡ መሆን አለባቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን አጭር ልቦለድ አንድ ታሪክ ብቻ ማንሳት አለበት፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለአሁኑ ታሪክ የሚያስፈልግ መረጃን ለማምጣት ሲል ደራሲው በምልሰት ቴክኒክ ወደኋላ ተመልሶ ሌላ ታሪክ ሊያስታውስ ይችላል፡፡ ይህ ግን በድርሰቱ ውስጥ ሁለት ታሪክ አለ ማለት አይደለም፡፡ ከጭብጥ አንፃርም ቢሆን የልቦለድ ታሪክ ከአንድ በላይ ጭብጥ ሊኖረው አይገባም፡፡

## የአጭር ልቦለድ ለመጻፍ የሚረዱ መንደርደሪያዎች

### ታሪክ

የልቦለድ መሰረታዊ ነገር ታሪክ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው በአጭር ልቦለድ ውስጥ ከአንድ በላይ ታሪክ ማካተት አይመከርም፡፡ ታሪኩ ቅደም ተከተል፣ ተአማኒነትና አጓጊነት ሊኖረው ይገባል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የታሪኩ ቅደም ተከተል ተገለባብጦ ወይም መጨረሻው መጀመሪያ፣ መሀለኛው መጨረሻ፣ መጀመሪያው ደግሞ መጨረሻ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ ይህም ታሪክ በልቦለድ ውስጥ የትኛውም ጊዜና ቦታ ላይ ሊጀምር እንደሚችል ያሳያል፡፡ ነገር ግን ታሪኩን የሚያያይዝ ሰንሰለት ይኖራል፡፡

ከታሪክ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ዋና ጉዳይ የቀረበው ታሪክ ተአማኒነት ነው፡፡ የምናቀረበው ታሪክ በአንድ ቦታና ጊዜ አንድን ድርጊት ሰዎች ሊያደርጉት ይችላሉ ወይ ወይም አንድ ነገር ሊሆን ይችላል ወይ ብለን ስንጠይቅ አዎንታዊ ምላሽ ሊያስገኝ የሚችል መሆን አለበት፡፡ ይህ በአብዛኛው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ግን ተአማኒነት የሌላቸውን ታሪኮች በአስደሳችነታቸው ብቻ ጥያቄ ሳናነሳ ልንቀበላቸው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በቀደምት ታሪኮች ውስጥ በዚህ ምድር ያልተከናወኑ ታሪኮች፣ ምትሀታዊ የሆኑ ድርጊቶች፣ በምድር የሌሉ ፍጡራን የተካተቱበት ታሪክ ልናገኝ እንችላለን፡፡ በዘመናዊ ልቦለድ ግን የተአማኒነት ጥያቄ ይነሳል፡፡ ስለሆነም ደራሲው ከአካባቢው ሁኔታ ጋር የሚስማማና ሊደረግ የሚችል ጉዳይ ላይ ተመርኩዞ ቢጽፍ ይመረጣል፡፡

በዚህ መልኩ ተቀናብሮ የሚፃፈው ታሪክ አጓጊ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በአጭር ልቦለድ ውስጥ በአንድ አንቀጽ ላይ የተፃፈ አጓጊ ነገር በሁለተኛው አንቀጽ ወይም ከዚህ ብዙ ሳይርቅ ይፈታል ምክንያቱም የጥድፊያ ባህሪው ስለሚያስቸኩለው ነው፡፡ የአጭር ልቦለድ ታሪክ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፈፀም አለበት፡፡

### ገጸባህሪ

የአጭር ልቦለድ ገፀባህሪያት በቁጥራቸው እጅግ የተመጠኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡ ቀደም ሲል ስለባህሪያቱ ባየንበት ክፍል የአጭር ልቦለድ ዋና ዋና ገጸባህሪያት ቢበዛ ከሁለት ማለፍ እንደሌለባቸው ከተቻለ ግን በአንድ ዋና ገጸባህሪ ላይ በማተኮር ታሪካችንን ማዋቀር እንዳለብን አይተናል፡፡ የታሪኩ መመጠን ወይም ነጠላ መሆን የገጸባህሪያትን ቁጥር እንድንመጥን ያስገድደናል፡፡ ዋናና ንዑስ ገጸባህሪያቱ ቁጥራቸው ብቻ ሳይሆን በታሪኩ ውስጥ የሚያከናውኑት ተግባርም ጭምር የተቆጠበ መሆን አለበት፡፡

> *አንድም ሆነ ሶስት ገጸባህሪያት ቢቀረጹም የሚፈጽሟቸው ድርጊቶችና ርስበርስ ያላቸው ግንኙነት ተመጥነው ይቀርባሉ፡፡ የሚገቡበትም ሁነት ውሱን በመሆኑ እንቅስቃሴያቸው በአያሌው የተመጠነ ይሆናል፡፡ ባሉበት ሁነት ውስጥ በተወሰኑ ድርጊቶች ሲሳተፉ ወይም አንድ ነገር ሲደርስባቸው ብቻ ይታያሉ፡፡ አጭር ልቦለድ ሰፊ ማህበረሰባዊ ህይወትን ስለማያሳይ የገጸባህሪያቱን ቁጥር መወሰኑ ብቻ ሳይሆን የገጸባህሪያቱን ሁለንተናዊ እድገትና ለውጥ ማሳየት ግዴታው አይደለም፡፡ ገጸባህሪያት ተወልደው ሲያድጉ፣ አድገው ሲኖሩ ኋላም አርጅተው ሲሞቱ አይታዩም፡፡ አጭር ልቦለድ ዋነኛው ገጸባህሪ አንድ ችግር ሲደርስበትና ይህኑ ለመወጣት ጥረት ሲያደርግና ሲወስን ብቻ ያሳያል እንጂ በተለያዩ ሁነቶች ውስጥ ገብቶ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ሲዳክርና ስቃዩን ሲበላ አያሳይም፡፡ ሌሎች ገጸባህሪያት ቢኖሩም ከሱው ጉዳይ ጋር በጠበቀ ቁርኝት የተሳሰሩና አንዳች ሚና የሚጫወቱ መሆን ይኖርባቸዋል(ዘሪሁን 1999፣231)፡፡*

ስለሆነም እያንዳንዱ የአጭር ልቦለድ ገጸባህሪ በአሳማኝ ምክንያት ሊቀረጽ ይገባዋል፡፡ በኋላም በታሪኩ ውስጥ የተቀረጸበትን ዓላማ ለማሳካት ብቻ ሲንቀሳቀስ መታየት አለበት ማለት ነው፡፡ ገጸባህሪያትን በማስተዋወቅ ጊዜ መፍጀት አይገባም፤ ቶሎ ወደ ዋናው ጉዳይ በመግባት በመንገድ

ላይ ስለገጸባህሪያቱ የተመጠነ መረጃ መስጠት ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር የሚሳሉት ገጸባህሪያት ሊታመኑ የሚችሉ ወይም ለእውነታ የቀረቡ መሆን አለባቸው፡፡ ፍፁማን የሆኑ ገፀባህሪያትን ላለመቅረጽ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**ግጭት**

በአንድ አጭር ልቦለድ ውስጥ አንድ ግጭት ብቻ ይኖራል፡፡ ግጭት ከሌለ ታሪኩ አጓጊነት አይኖረውም እንዲያውም ታሪኩን ወደፊት የሚያስኬደው ግጭት ነው፡፡ ግጭቱን ስንመሰርት ተፋላሚ ሀይላቱን ተመጣጣኝ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ሀይላት ሀሳቦች፣ ሰዎች ወይም ሰውና ተፈጥሮ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ተመጣጣኝነታቸው በአስተሳሰብ፣ በአቀራረብና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ጎልማሳና አንድ ህፃን ልጅን ለፍልሚያ ብናቀርብ ታሪኩ ተአማኒነትን ሊያጣብን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ ሀይላት በአካላዊም ሆነ ህሊናዊ ብቃት የማይመጣጠኑ በመሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህ ተቃራኒ ሀይላቱ በሆነ ገጽታቸው ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው፡፡ የሁለት ወጣቶች ግጭት አሳማኝ ሊሆን ይችላል፣ ቢያንስ በእድሜ ተቀራራቢ ስለሚሆኑ፡፡

ከዚህ በኋላ እነዚህን ተመጣጣኝ ሀይላት ሊያጋጭ የሚችል አሳማኝ መንስኤ ግጭት መጠንሰስ ያስፈልጋል፡፡ ከላይ በተሰጠው ምሳሌ ላይ ሁለቱ ወጣቶች በገንዘብ ተጣሉ ብንል የገንዘብ ጉዳይ የግጭታቸው መንስኤ ሆነ ማለት ነው፡፡ በዚህ አይነቱ መንስኤ የተነሳው ግጭት ተፋፍሞ ተመጣጣኝ ሀይላት ሲፋለሙ መታየት አለባቸው፡፡ መንስኤ ግጭቱ በፈጠረው አለመግባባት ምክንያት የተፈጠረው ፍልሚያ ምናልባት በመከራከር ጀምሮ ከዚያ ወደ ጭቅጭቅ ከፍ ሲልም ወደ መሰዳደብ ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡ ፍልሚያው የመጨረሻ ደረጃ ላይ ሲደርስ (ይህ ደረጃ ምናልባት ድብድብ ሊሆን ይችላል) በአንድ ምክንያት እየበረደ ይመጣል፡፡ ይህ ምክንያት የአንደኛው ወገን አሸናፊነት ሊሆን ይችላል፡፡

በመጨረሻም ፍልሚያው ሲጠናቀቅ በተፋላሚዎች ላይ የሚታይ ለውጥ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ሁለቱ ወጣቶች አካላዊ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል፣ ተሸናፊው አዝኖ አሸናፊው ሊደሰት ይችላል ወይም ቂጣቸውን በድብድብ ካበረዱ በኋላ ተስማምተው ከንዘቡን ለመካፈል ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ እንግዲህ በአጭር ልቦለድ ውስጥ ይህ ሁሉ የግጭት ደረጃ በፍጥነት መከናወን የሚገባው ሲሆን አቀራረቡም በጣም የተቆጠበ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ጥድፊያውን ስኬታማ ለማድረግ ሲባል ከአንድ በላይ ግጭት በታሪኩ ውስጥ ማስገባት አይመከርም፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከአንድ በላይ ግጭት የምናካትት ከሆነ ግን ታሪኩ ይንዛዛና የአጭር ልቦለድነት ባህሪውን ያሳጣዋል፡፡

**መቼት**

የአጭር ልቦለድ መቼት ጠባብ ነው፡፡ ከአንድ የተወሰነ ጊዜና ቦታ ብዙ ርቆ አይሄድም፤ እንዲያውም ብዙ ጊዜ በተጀመረበት ቦታ ያልቃል፡፡ ቤት ውስጥ ከተጀመረ ቤት ውስጥ ያልቃል አልያም በአቅራቢያው ወደሚገኝ ሌላ ስፍራ ሊሻገር ይችላል፡፡ ታሪኩ የሚወስደው ጊዜም ቢሆን እንዲሁ አጭር ነው፡፡ አንዳንድ የአጭር ልቦለድ ታሪኮች የደቂቃዎች ብቻ እድሜ አላቸው፡፡ የሰዓታት፣ የቀናት አለዚያም የሳምንታት

እድሜ ያላቸው ታሪኮችንም ልናገኝ እንችላለን፡፡ ከዚህ ውጪ ግን አገር አቋርጦና ዘመን ተሻግሮ ታሪክን መተረክ የአጭር የልቦለድ ባህሪ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ በአጭር ልቦለድ ውስጥ አላባውያኑ ከላይ ያለውን መልክ ይዘው እንደ የመቼትና የገጸባህሪያት ገለፃ፣ ምልሰትና ንግር እንዲሁም ምልልስን በመሳሰሉ የአተራረክ ዘዴዎች አማካኝነት ተሳስረው ሊቀርቡ ይገባቸዋል፡፡ የአተራረክ ዘዴዎቹም ቢሆን የቁጥብነትና ጥድፊያ ባህሪውን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው፡፡ ለምሳሌ በረጅም ልቦለድ ውስጥ እንደምናገኛቸው ዓይነት ያሉ ሰፋፊ የመቼትና የገጸባህሪያት ገለፃዎችን፣ ረጃጅም ህልሞች ወይም የገጸባህሪያት ምልልሶችን፣ የገጸባህሪያትን የህይወት ውጣውረድ ከልደት እስከሞት የሚያሳዩ ትረካዎችን ለማካተት የሚያስችል የጊዜም ሆነ የቦታ አቅም አጭር ልቦለድ የለውም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ነገር ተመጥኖ መቅረብ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

## ሐ. ረጅም ልቦለድ

ረጅም ልቦለድ ረጅም፣ ዝርውና ተራኪ የሆነ የፈጠራ ጽሑፍ ዘር ነው፡፡ ርዝማኔና ተራኪነቱ ላይ በማተኮር ጌታቸው በለጠ ስለረጅም ልቦለድ ያለውን አስተያየት በሚከተለው መልኩ አስፍሯል፡፡

> *ከማህበረሰቡ የህይወት ምንጭ መንጭቶ፣ በበርካታ የህይወት ልምምድ ገባሮች እየጎለበተ፣ በኑሮ ውጣ ውረድ ተራሮችና ሸለቆዎች እየወደቀና እየተነሳ፣ ከአንዱ የቆረሰውን ሕይወት፣ ለሌላው ጥቅም እንዲሆን እያጎረሰ፣ የአንዱን ገጸባህሪ ህይወት እያለመለመ ወይንም የሌላኛውን ገጸባህሪ ህልውና እያጨለመ፣ እንደ ድርና ማግ የሰው ልጆችን የውስጥና የውጭ ሰብዕና በመሸመን ረጅም ልቦለድ ሚናውን ይወጣል(2004፣185)፡፡*

ረጅም ልቦለድ በባህሪው ከአጭር ልቦለድ ፍፁም ተቃራኒ በሆነ መልኩ የሚጓዝ ነው፡፡ ሰፊ ታሪክን ማካተት የልቦለድ ዋነኛ ባህሪ ነው፡፡ ሰፊ ታሪክን በመያዙ ምክንያት ደግሞ ገጸባህሪያቱም ብዙ ናቸው፡፡ ታሪኩም ቢሆን በግጭት የተሞላ በመሆኑ ገጸባህሪያቱ በበርካታ ግጭቶች ውስጥ እየገቡ ሲፋለሙ ይታያሉ፡፡ መቼቱም እንዲሁ እጅግ የተስፋፋ በመሆኑ አገር አቋርጦና ድንበር ተሻግሮ የገጸባህሪያትን ታሪክ ከልደት እስከሞት የመተረክ አቅም አለው፡፡ ከዚህ ውጪ ግን በአጭር ልቦለድ ውስጥ የምናገኛቸውን አላባውያን በመስፋፋታቸው ከመለያታቸው በስተቀር በረጅም ልቦለድ ውስጥም እናገኛቸዋለን፡፡ የአተራረክ ዘዴዎቹንም በአጭር ልቦለድ ውስጥ በሚይዙት የተመጠነ ቅርፅ ሳይሆን በጣም በተስፋፋ መልኩ ረጅም ልቦለድ ውስጥ እናገኛቸዋለን፡፡ ስለሆነም እነዚህን አላባውያንና የአተራረክ ዘዴዎች ከመተንተን ይልቅ በቀጥታ ረጅም ልቦለድን እንዴት መፃፍ እንደምንችል ወደማየቱ እናልፋለን፡፡

### ረጅም ልቦለድ ለመፃፍ የሚረዱ መንደርደሪያዎች

ልቦለድ ሲፃፍ የሂደቱ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ታሪኩ እንዲሁ በብዙ ርዕሰ ጉዳዮችና ገጸባህሪያት ዙሪያ ይሽከረከራል፡፡ ቅርጽ እየያዘ የሚመጣው ፀሐፊው ደግሞ ደጋግሞ ስለጉዳዩ ካብላላ በኋላ ነው፡፡ “መፃፍ ህይወትን ሰርስሮ በመዝለቅ ለመመርመር የሚደረግ ሙከራ ነው፡፡ ጀማሪ ደራሲያን ደግሞ ምርምራቸውን መጀመር ያለባቸው የገዛ አእምሯቸው ውስጥ ከሚመላለሰው ሀሳብ ነው፡፡” (Goldberg 1986, 5-7) ስለሆነም ረጅም ልቦለድ የመፃፍ የመጀመሪያው ደረጃ ስለምንጽፈው ታሪክ በሚገባ ማሰብ ይሆናል፡፡

ልቦለድ በመፃፍ ሂደት ውስጥ ከመነሻው የጥሩ ታሪክ መኖር የመጨረሻው ስራ ስኬታማ ሊሆን እንደሚችል አመላካች ነው፡፡ ለልቦለድ የምንመርጠው ታሪክ በጥንቃቄ መመረጥ አለበት፡፡ አዘውትሮ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እንደሚነገረው ታሪክ በቅደም ተከተል የተደረደሩ ሁነቶች ዘገባ ነው፡፡ የብዙ ሰዎችን ታሪክ እናውቅ ይሆናል፡፡ የለት ተለት ህይወታችንም በታሪክ የተሞላ ነው፡፡ በፈጠራ ስራ ውስጥ ሲሆን ግን ታሪክ በምናብ ሀይል የተፈጠረና ብዙ ድንቆችን የያዘ ይሆናል፡፡ በልቦለድ ውስጥ ታሪክ አንድ ገጸባህሪ በመንገዱ የሚያጋጥሙትን መሰናክሎች አልፎ እንዴት ያለመው ግብ ላይ እንደሚደርስ የሚነግር ነው፡፡

የተለያዩ ታሪኮች አሉ፡፡ ለምሳሌ የፍቅር፣ የጦርነት፣ የረሀብ፣ የጀግንነት… ወዘተ፡፡ የለት ተለት ህይወታችን የታሪክ ምንጭ ሊሆንልን ይችላል፡፡ አለያም ከቀደሙ ታሪኮች መካከል ለፈጠራ ስራችን ልንወስድ እንችላለን፡፡ ከነዚህ አማራጮች መካከል የምንጸፍበትን ታሪክ በጥንቃቄ ማምረጥ አለብን፡፡ በታሪክ መረጣ ሂደት ውስጥ ከእለት ተለት ህይወትም ሆነ ከቀደሙ ታሪኮች የፈለግነውን ታሪክ መርጠን የመተቀም ነፃነት አለን፡፡ ነገር ግን በአንድ ደራሲ የተፃፈን ታሪክ ደግሞ መጠቀም ተጠያቂነትን ያመጣል፡፡

መነሻ የሚሆነንን ታሪክ ከመረጥን በኋላ ቀጣዩ ስራ የሚሆነው በዚያ ታሪክ ላይ ተመርኩዘን የራሳችንን ታሪክ ማዳበር፣ ሴራ መጠንሰስ፣ ገጸባህሪያትን መቅረጽ… ይሆናል፡፡ አንድ የልቦለድ ታሪክ በጥሩ ሁኔታ እንዲጀምር ከተፈለገ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ደራሲው በሚገባ ሊያስብበት ይገባል፡፡ ይህን በማድረግም ታሪኩ ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄድና በየደረጃው የት እንዳለ ወደፍፃሜውም እንዴት እንደሚደርስ ማወቅ ይቻላል፡፡

ታሪካችንን ስናደራጅ/ቅርጽ ስናሲዝ መግለጽ የምንፈልጋቸውን የሰው ልጅ ገጠመኞች እያሰብን መሆን አለበት፡፡ ታሪኩ ቅርጽ እየያዘ ሲሄድ ደራሲውም ስለአካሄዱ ያለው እይታ ይበልጥ ግልጽ እየሆነ ይመጣል፡፡ ቅርጽ መንገር የተፈለገውን ታሪክ የተለያዩ ክፍሎች አንድ ላይ ያያይዝልናል፤ የታሪክ ማስፋፊያ ሀሳቦችን ለማመንጨትም ይረዳል፡፡ በአጠቃላይ ቅርፁ ከተስተካከለ ከየት ተነስተን በየት አልፈን የት እንደምንደርስ እናውቃለን፡፡

የገጸባህሪያት ግጭት ታሪክን ይፈጥራል፣ ወደፊትም ያራምዳል፡፡ ታሪክ በደስታና መልካም ነገሮች ብቻ የተሞላ ሊሆን አይችልም፡፡ ለገጸባህሪያቱ ጉዞ እንቅፋት የሚሆኑ መሰናክሎች መኖር አለባቸው፣ ድርጊቶችም ፈተናዎችን መውለድ አለባቸው፡፡ ደስታ፣ ፍቅር፣ ድል… ከሀዘን፣ ጥላቻ፣ ሽንፈት… ጋር ተደባልቀው መቅረብ አለባቸው- የእውኑ አለም እንዲህ ስለሆነ፡፡

**የረጅም ልቦለድ ትልም አነዳደፍ**

አንድ ረጅም ልቦለድ ከመፃፋችን በፊት በቅድሚያ ትልም መንደፍ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ማድረግ ከላይ እንደተገለጸው ታሪኩን ቅርጽ ለማስያዝና ከየት ተነስቶ የት እንደሚደርስ ለማወቅ ይረዳል፡፡ ትልም ለመንደፍ በቅድሚያ መነሻ የሚሆን ታሪክ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የአንድ ድሀ ቤተሰብ ታሪክ፣ የአንዲት ብቸኛ ሴት ህይወት ወይም ሌላ መሰል ታሪክ ሊሆን ይችላል፡፡ መነሻ የሚሆነንን

ታሪክ ካገኘን በኋላ ቀጣዩ ተግባር ትልሙን መንደፍ ነው፡፡ የታሪካችንን ትልም በምንነድፍበት ጊዜ ሀሳባችንን መቆጣጠር መቻል አለብን፡፡ እጅግ በርካታ ሀሳቦች ተደራርበውብን ትልሙ ይመሰቃቀልና ታሪኩ ከየት ተነስቶ በየት አልፎ የት እንደሚደርስ ከማሳየት ይልቅ ውስብስብና ግራ አጋቢ የሆነ ነገር ልንፈጥር እንችላለን፡፡ ስለሆነም የምናካትተውን እያንዳንዱን ሀሳብ ከታሪኩ ጋር በምን ዓይነት መልኩ ልተሳሰር እንደሚችልና ምን ፋይዳ እንደሚኖረው በትኩረት መፈተሽ አለብን፡፡ በዋናው ታሪካችን ውስጥ ሌሎች ትንንሽ ታሪኮችን መንገር የምንፈልግ ከሆነም ይህን ስናደርግ በጥንቃቄና ባለው መልኩ መሆን አለበት፡፡

የትልም አነዳደፍ ሂደቱን ቀላል ለማድረግ የሚከተሉት ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ነው፡፡

- ለታሪኩ ግብ ማበጀት

ግብ ዋናው ገጸባህሪ ያሳካው የሚፈልገው አላማ ወይም ሊፈታው የሚፈልገው ችግር ነው፡፡ ይህ አላማ በታሪኩ ውስጥ ያሉ ሌሎች ገጸባህሪያት ላይም ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በአጠቃላይ የታሪኩ ማጠንጠኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ስለአንዲት ስራ ስራዬን ስትል ሳታገባ የቆየችና አሁን ግን በዚህ ጉዳይ መፀፀት የጀመረች የ35 አመት የቢሮ አራተኛ ታሪክ መፃፍ ብንፈልግ የታሪኩ ግብ ይቺ ሴት እውነተኛ የፍቅር ጓደኛ እንድታገኝ ማድረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ሌሎቹን ገጸባህሪያት በተመለከተ ደግሞ ለምሳሌ የልጇን ደስታ ማየት የምትናፍቅ እናት፣ በጣም ደስተኛ የሆኑ ጥንዶች (ላጤዋን ለትዳር የሚያነሳሱ)፣ የገጸባህሪዋ ጎረቤት የሆነ መልከመለካም ወንደላጤ፣ ያላገባችና ህይወቷን በስተርጅና በብቸኝነት የምትገፋ የዋናዋ ገጸባህሪ አክስት… ልንፈጥር እንችላለን፡፡ እነዚህ ሁሉ ለግቡ መሳካት አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ ለታሪኩ ግብ ማበጀት በትልም መንደፍ ተግባር ውስጥ ዋነኛውና የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡

- ጦስ

ይህ የታሪኩ ግብ መሳካት ባይችል ሊፈጠር የሚችለው ምስቅልቅል ነው፡፡ የግብና የጦስ ጥምረት በልቦለድ ውስጥ ዋናውን ውጥረት የሚፈጥረው ጉዳይ ነው፡፡ ከላይ በቀረበው የታሪክ መነሻ ሀሳብ ላይ የተቀመጠው ግብ ሳይሳካ ቢቀር ሴትየዋ የአክስቷ እጣ ፈንታ ይደርሳታል፡፡ ስለዚህ ትዳር ለመመስረት የሚደረገው ሙከራ አለመሳካት ጦስ ሊሆን ይችላል፡፡

- ግቡን ወደስኬት ለመውሰድ የሚያስፈልጉ ክንውኖች

እነዚህ ግቡ ከዳር ይደርስ ዘንድ ዋናው ገጸባህሪ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ድርጊቶች ናቸው፡፡ ይህንን በዝርዝር ለይቶ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ የታሪኩን ፍሰት ተከትሎ ገጸባህሪው እነዚህን ድርጊቶች ሲፈጽም አንባቢው ገጸባህሪው ወደ ግቡ እየቀረበ እንደሆነ ያስባል፡፡ በምሳሌያችን ውስጥ ግቡን ወደ ስኬት ለመውሰድ ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ ሴትዮዋ ወንዶችን ለመቅረብና ለመተዋወቅ ጥረት ማድረጓ ሊሆን ይችላል፡፡

- ማስጠንቀቂያዎች

ማስጠንቀቂያዎች ጦስ እየቀረበ እንደሆነ ምልክት የሚሰጡ የታሪኩ ክፍሎች ናቸው፡፡ ማስጠንቀቂያዎች ካሁን አሁን ገጸባህሪው ግቡን ሳያሳካ ተሰናክሎ ቀረ የሚል ስሜትን የፈጥራሉ ስለዚህ አንባቢያንን በስጋት ይንጣሉ፡፡ ምሳሌያችን ባደረግነው ታሪክ ውስጥ ጦስ መቅረቡን ለማመልከት የሚከተሉት ክስተቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡

- ሴትዮዋ የሚያጋጥሟት ወንዶች ሁሉ መጥፎዎች ይሆናሉ
- አንድ የሴትየዋ ጓደኛ በከፍተኛ ጥል ከባሏ ትፋታና ገጸባህሪዋ ትዳር የማያዋጣና ዘላቂ ደስታ የማይገኝበት ነው ብላ ልታስብ ትችላለች

በዚህ ሁኔታ ለግብ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ክንውኖችና ማስጠንቀቂያዎች እየተፈራረቁ አንባቢውን አንዴ እያስፈራሩና እያስጨነቁ ሌላ ጊዜ ደግሞ እያስደሰቱና ተስፋ እየሰጡ ያዋልሉታል፡፡

- ዋጋ

በጥሩ ልቦለድ ውስጥ ሴራ የችግሮች ቋት ነው፡፡ እነዚህ ችግሮች ደግሞ ለገጸባህሪያቱ አንገብጋቢ ናቸው፡፡ ስለዚህ ለዋናው ገጸባህሪያችን ግድ ኖሮት ችግሩን ለመፍታት ጥረት ያደርግ ዘንድ የሚያንገበግብ ችግር ልናጋፍጠው ይገባል፡፡ ገጸባህሪው ይህን ችግር ለመፍታት የሚከፍለው መስዋእትነት ዋጋ ይባላል፡፡ በምሳሌያችን ውስጥ ያለቸው ገጸባህሪ የተረጋጋ ትዳር ለመመስረት ስትል ስራዋን ለመልቀቅ ብትወስን ስራዋን መልቀቋ ለትዳር ስትል የከፈለችው ዋጋ ይሆናል ማለት ነው፡፡

- ድርሻ

ድርሻ ለሁሉም ገጸባህሪ በታሪኩ መጨረሻ እንደየስራው የሚከፈለው ክፍያ ነው፡፡ ሁሉም የድርሻውን ያገኛል፡፡ ይህ ድርሻ ገጸባህሪያቱ ግቡን ለማሳካት ሲሉ የሚያደርጉት ሩጫና መውደቅ መነሳት ውጤት ነው፡፡ በምሳሌያችን ውስጥ ሴትዮዋ እውነተኛ ፍቅርን ለማግኘት ባደረገችው ሩጫ ልቧ ሊለወጥና ለሰዎች የምትራራና በቀላሉ ሰዎችን የምትቀበል ልትሆን ትችላለች፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ስድስት ጉዳዮች መሰረት አድርገን በምሳሌነት የተጠቀምንበትን መነሻ ታሪክ ትልም ብንነድፍ የሚከተለውን መልክ ሊይዝ ይችላል፡፡

አንዲት የ35 ዓመት ሴት ስራዋን ባሏ አድርጋ ትኖር ነበር፡፡ እድሜዋን ሙሉ በብቸኝነት ያሳለፈችው አክስቷ በአሳዛኝ ሁኔታ በምትሞትበት ጊዜ ድንገት ህይወቷ ባዶ መሆኑ ይሰማታል፡፡ ከዚያም ይህቺ ሴት መጨረሻዋ እንደ አክስቷ እንዳይሆን በመስጋት አግብታ ቤተሰብ መመስረት እንዳለባት ትወስናለች፡፡ በዚህም መሰረት ከአንዳንድ ወንዶች ጋር መተዋወቅና መቀራረብ ትጀምራለች፡፡ ከተዋወቀቻቸው ወንዶች መካከልም ከአንዱ ጋር መልካም ግንኙነት ትመሰርታለች፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለች አለቃዋ ካለችበት ከተማ ወደሌላ ከተማ መዘዋወርን ግድ የሚል እድገት ይሰጣታል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሰው ጋር የጀመረችውን አስደሳች ግንኙነት የሚያቋርጥባትና ህልሟን መና የሚያስቀርባት ጉዳይ በመሆኑ እድሜዋን ሙሉ የደከመችለት ስራዋ ቢሆንም እድገቱን አልቀበልም ትላለች፡፡ በመጨረሻም የቀረበችው ወንድ ከልቡ ያፈቅራትና ከዚህ ሰው ጋር ትዳር ትመሰርታለች፡፡

## መ. ተውኔት

ዝነኛው የግሪክ ፈላስፋ Arstotle “Drama” የሚለውን ቃል በመድረክ ላይ በተመልካች ፊት የሚተወንን ግጥማዊ ስራ ለመግለጽ ተጠቅሞበታል፡፡ በዘመናችንም ቢሆን ድራማ/ተውኔት በመድረክ ላይ በትወና መልክ እንዲቀርብ ታስቦ የሚፃፍ የስነጽሑፍ ዘርፍ በመሆኑ ይታወቃል፡፡ ተውኔት የሰው ልጆችን የእለት ተእለት ገጠመኝ በመቅዳትና በማስመሰል ላይ ተመስርቶ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚመደረክ ታሪክ ነው፡፡ ስለሆነም በየትኛውም ባህል ውስጥ ዋነኛ የባህሪ መግለጫ እንዲሁም የሰዎችን ስሜት የሚመረምርና የሚያንፀባርቅ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ተውኔት እውናዊና ምናባዊ የሆኑ ክስተቶችን በትወና መልክ በማቅረብ ግለሰቦችና ቡድኖች የተለያዩ ሀሳቦችንና ስሜቶችን ተውኔታዊና ተምሳሌታዊ በሆነ መልኩ እንዲመረምሩና ቅርጽ እንዲያሲዙ የሚያስችል የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡

ከባህሪው አንፃር ተውኔት የስሜት ንረት ጎልቶ የሚታይበትና አብዛኛውን ጊዜ ሰብአዊ የሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር የፈጠራ ጽሑፍ ነው፡፡ በመሆኑም እውናዊውን አለም ወክለው ከህይለኛ ስሜት ጋር ቁርኝት ያላቸው ገጠመኞችን በህይወታቸው የሚያስተናግዱ ገፀባህሪያትን መቅረጽ ላይ ያተኩራል፡፡ ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘሮች ተለይቶ በተመልካች ፊት በመድረክ እንዲቀርብ ታስቦ ይጻፋል፡፡ ድርጊትን በመድረክ ላይ ስለሚያቀርብም ከሌሎቹ የስነጽሑፍ ዘሮች ይበልጥ ለስሜታችን ቅርብ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የተደራሲውን ትኩረት የመሳብ ልዩ ሀይል አለው፡፡

ተውኔት የሰው ልጅን ሁለንተናዊ የአኗኗር ሁኔታ ነፍስ ዘርቶ ያሳያል፡፡ በዚህም የተነሳ ለዋጭነቱ ወይም በሰው አእምሮ ውስጥ አንዳች ነገር ቀርጾ የማስቀረት አቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ በሌላም በኩል ድርጊታዊነት ይበዛበታል፡፡ ተዋንያኑ ድርጊት ይፈጽማሉ፣ ተመልካቹም በድርጊት ይሳተፋል (ይስቃል፣ ያለቅሳል…)፡፡ እንደ ረጅምና አጭር ልቦለድ ስለገጸባህሪያቱ ድርጊት አይተርክም በድርጊት ያሳያል እንጂ፣ ስለዚህ ገጸባህሪያቱን በህሊና ሳይሆን በገሀዳዊው አይናችን እናያቸዋለን፡፡

**የተውኔት አላባውያን**

አብዛኞቹ የተውኔት አላባውያን ከልቦለድ አላባውያን ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ በመሰረታዊ ባህሪያቸውም ብዙ ልዩነት አይታይባቸውም፡፡ Arstotle ስድስት የተውኔት አላባውያንን ይጠቅሳል፡፡ እነዚህም ሀሳብ (thought)፣ ሴራ (plot)፣ ገጸባህሪ (character)፣ ቃለተውኔት/ቋንቋ (language)፣ ሙዚቃ (music) እና ትዕይንት (spectacle) ናቸው፡፡ (Poetics 1998) የሀገራችን ጸሐፊ ፋንታሁን እንግዳ ደግሞ የArstoteን ጨምሮ የተለያዩ ጸሐፍትን ሀሳብ ከተመለከተ በኋላ የዘመናችን ሃያስያንና ጸሐፊ ተውኔቶች በቀደሙት ሀሳብ ላይ ማሻሻያዎችን በማድረግ የተውኔት አላባውያንን በአምስት (መቼት፣ ገጸባህሪ፣ ሴራ፣ ቃለ ተውኔትና ጭብጥ) ከፋፍለው እንደሚያስቀጧቸው ይናገራል፡፡ (2005፣11) ከቃለተውኔት በስተቀር እነዚህ አላባውያን ከፍ ብሎ እንከተገለጸው ከልቦለድ አላባውያን ጋር በእጅጉ የሚመሳሰሉ ቢሆኑም አንዳንድ ልዩ የሚያደርጋቸው ባህሪያቸው ላይ በማተኮር ጠቅለል አድርገን እንመለከታቸዋለን፡፡

መቼት በተውኔት ውስጥ ቦታና ጊዜን የሚያመለክት ጉዳይ ሆኖ በውስጡ ታሪካዊ ጉዳዮችን፣ መልክዓምድራዊ ትዕይንቶችን፣ የተፈጥሮ ክስተቶችን (ምሽትና ንጋትን፣ ክረምትና በጋን)፣ ማህበራዊና

ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በመያዝ የአንድ ተውኔት ታሪክ የትና መቼ እንደተፈፀመ ያስረዳናል፡፡ ተውኔቱ በመድረክ ከቀረበ ይህንን መቼት መድረኩ ላይ በሚገነቡ ግንባታዎች፣ ቅቦች ወይም መብራቶች አማካኝነት በአይናችን እናየዋለን፡፡

በተውኔት ውስት ገጸባህሪያት ከልቦለዶች ለየት ባለ ሁኔታ ለአንባቢው ሊተዋወቁ ይችላሉ፡፡ የኸውም የቃለ ተውኔቱ አካል ባልሆኑ የፊት ገጾች ላይ በተውኔቱ ውስጥ የሚሳተፉ ገጸባህሪያት ተዘርዝረው ይቀርባሉ፡፡ ተውኔት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተከውኖ እንዲያልቅ ታስቦ የሚፃፍ ጥበብ በመሆኑ የገጸባህሪያት ቁጥር መመጠን አለበት፡፡ አለዚያ ግን የተውኔቱ ሴራ እጅግ ይስፋፋና አሰልቺና የተንዛዛ ይሆናል፡፡ በተውኔት ውስጥ የሚሳሉትን ገጸባህሪያት በመድረክ ላይ ተላብሰው የሚቀርቡ ተዋንያን በምናብ የተሳሉትን ገጸባህሪያት ህይወት ዘርተው ወደ እውናዊው አለም የማምጣት ከፍተኛ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ሴራና ጭብጥ በተውኔት ውስጥ በልቦለድ ከምናውቀው ብዙም የተለየ ገጽታ የላቸውም፡፡

ቃለተውኔት ተውኔትን ከሌሎች የስነጽሑፍ ዘሮች የሚለየው አላባ ነው፡፡ በተውኔት ውስጥ በዋናነት ሁለት አይነት የቋንቋ አጠቃቀሞች ሲኖሩ የመጀመሪያው ቃለ ተውኔት ሁለተኛው ደግሞ የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ ነው፡፡

የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫ የጸሐፌ ተውኔቱ የቋንቋ አጠቃቀም የሚታይበት፣ ተውኔት ሲመደረክ መቼቱን ባገናዘበ መልኩ ገጸባህሪያቱ የሚያደርጉትን ድርጊት የሚጠቁም ስለገጸባህሪያቱ አካባቢያዊ ሁኔታ ጥቆምታ የሚሰጥበት ቋንቋ ነው፡፡ የመድረክ እንቅስቃሴ መግለጫዎች የገጸባህሪያቱን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ከመግለጽ ባሻገር ጊዜ፣ ቦታ፣ ድርጊት፣ እንቅስቃሴ፣ መውጣትና መግባት፣ ግባተ ድምጽና የመድረክ ቁሳቁስ፣ አልባሳት አካላዊ አቋም… የመሳሰሉትን ለመግለጽ ይጠቅማሉ፡፡ በተውኔቱ ላይ ለሚሳተፉ ባለሙያዎች በሙሉ ነገሮችን እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው መነሻ ይሰጣቸዋል፡፡

ቃለ ተውኔት በአንድ ተውኔት ውስጥ የተሳሉ ገጸባህሪያት ከአንደበታቸው አፍልቀው በዝርው፣ በግጥም ወይም በዝርውና በግጥም የሚያደርጉት ንግግር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ተጫኔ፡-  (ፊቱ በቅጽበት ከቁጣ ወደ ፈገግታ ይለወጣል) ኧረ ያርባራቱ ታቦታት ያለህ! ገዝሙ! (ይንደረደርና እጆቹን ከገዝሙ ትከሻና ተከሻ ያሳርፋል፣ ወዲያው ጉንጭና ጉንጩንይስመዋል፡፡ ገዝሙ ግን አጸፋውን አይመልስም) እንደምን አለህ ገዝማቸው? ደህና ነህ፣ ገዝምነት? (የተውኔት ጉባኤ 1957፣122)

ከላይ በቀረበው ምሳሌ ውስጥ በቅንፍ ውስጥ የቀረበው የመድረክ መግለጫ ሲሆን ከቅንፍ ውጪ ያው ደግሞ ቃለ ተውኔት ነው፡፡ ቃለ ተውኔት በሶስት አይነት ቅርጽ ሊገኝ ይችላል፡፡

1. *ምልልስ፡- ሁለትና ከዛ በላይ የሆኑ ገጸባህሪያት የሚያደርጉት የእርስ በእርስ የሀሳብ ልውውጥ ነው፡፡ ተዘውታሪና ብዙውን የቃለተውኔት ቦታ የሚሸፍን ነው፡፡*
2. *ንባበ አእምሮ፡- አንድ ገጸባህሪ/ተዋናይ ብቻውን ሆኖ ከራሱ ጋር የሚነጋገርበት ቅርጽ ሲሆን ጸሐፌ ተውኔቱ ገጸባህሪያት በአእምሯቸው ውስጥ የሚያሰላስሉትን ሀሳብ ለመግለጽ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው፡፡*
3. *ጎንታ፡- አንድ ገጸባህሪ፣ ተዋናይ ሌላው ገጸባህሪ ተዋናይ ሊሰማው በማይችል ቦታ እንደቆመ ታዛቢ ተደርጎ ስለሌላው ወይም ስለሌሎቹ የሚናገረውና ተደራሲው ብቻ እንዳደመጠው ተቆጥሮ የሚቀርብ የቃለ ተውኔት አይነት ነው፡፡*

**የተውኔት አፃፃፍ**

ቃለተውኔት በተውኔት ውስጥ ድርጊት ማለት ነው፡፡ በዘፈቀደ ወይም ጽሑፉን ለማሳመር ሲባል የሚገባ አይደለም ሁልጊዜም ቢሆን አላማ ኖሮት ነው የሚፃፈው፡፡ ታሪኩን ወደፊት ያራምዳል፣ የገጸባህሪያቱንም

ማንነት በየደረጃው ይበልጥ እያሳወቀ ይሄዳል፡፡ የምንጽፈው ተውኔት ያሰፈርናቸውን ድርጊቶች በሚተውኑ ተዋንያን፣ የገለጽናቸውን የመድረክ መግለጫዎች በሚገነዘቡ አዘጋጆችና መድረክ ገንቢዎች በትብብር የሚሰራ ነው፡፡ በመሆኑም የምንጽፈው ነገር መመሪያ ነው ማለት ነው፣ ሌሎች መመሪያውን ተከትለው እኛ መንገር የፈለግነውን ታሪክ ማቅረብ የሚያስችላቸው መመሪያ፡፡ ከዚህ የተነሳ መመሪያዎቻችን ግልጽና ትክክለኛ ሊሆኑ ይገባል፡፡

በተደራሲያኑም በኩል ቢሆን ከባድና የተወሳሰበ ቃለተውኔት ሲሰሙና ሳይገባቸው ሲቀር ተዋንያኑን አስቁመው ሀሳቡን ማስደገም ወይም ሀሳቡን የሚያብላሉበት ጊዜ ማግኘት ስለማይችሉ በተቻለ መጠን ግልጽ ሆኖ ሊሰፍር ይገባዋል፡፡ ተውኔታችንን ስንጀምር ገጸባህሪያቱን በማስተዋወቅ መሆን አለበት፡፡ በተውኔቱ መጀመሪያ ላይ የገፀባህሪያትን ዝርዝር ማስፈር፣ ከዝርዝሩ ጋርም ለያንዳንዱ ገጸባህሪ ጥቂት መረጃ ማከል ተገቢ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይህ በአንድ ወይም ሁለት ቃላት ሊከናወን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የመንግስቱ ለማ (1957) "ባለካባና ባለዳባ" ተውኔት ገጸባህሪያት በሚከተለው መልኩ ተዘርዝረዋል፡፡

*ገዝሙ፡- ምሁር*
*ተጫኔ፡- ባለስልጣን*
*ቢቢታ፡- የገዝሙ እጮኛ*
*ጂልሰን፡- የት/ቤት ዲሬክተር*
*ደጀኔ፡- የተጫኔ ባለሟል*
*የገዝሙ አባት*
*የሆቴል አሳላፊ፣*
*የሆቴል ባሪስታ፣*
*የተጫኔ ዘበኛ፣*
*የተማሪ ቤት አሳላፊዎች፣*
*የተጫኔ ሾፌር፣*

ሁል ጊዜ መድረክ ላይ ማን እንዳለ መጥቀስ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ በአብዛኛው በመድረክ መግለጫው ውስጥ ይካተታል፡፡ እያንዳንዱ ገጸባህሪ ወደ መድረክ የሚገባበትና የሚወጣበት ጊዜ በግልጽ መቀመጥ አለበት፡፡ እዚህ ላይ አስፈላጊ ከሆነ የአገባቡንና አወጣጡን ሁኔታ ጨምሮ መግለጽ ይቻላል፡፡

በቃለ ተውኔቱ ውስጥ አጽንኦት የሚያስፈልጋቸውን ቃላትና ሀረጎች ወይም በተለያየ ድምጸት መነገር የሚገባው የቃለተውኔቱ ክፍል ካለ በመድረክ መግለጫው ውስጥ ለዚሁ የሚሆን መመሪያ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ አንድ ገጸባህሪ ሲደሰት፣ ሲያዝን፣ ሲቆጣ፣...ድምፁ ተማሳሳይ ቃና አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ተደራሲው የገጸባህሪያቱን ስሜት መረዳት ይችል ዘንድ የድምጽ ቃናው ተለይቶ ሊካተት ይገባዋል፡፡

ምሳሌ፡- ተጫኔ፡- (በማስፈራራት ድምጽ) ስሙኝ ጌታዬ--?

እርስዎን እኮ ነው!

ከዚህ ጋር ተያይዞ ቃለተውኔቱ ከድርጊት ጋር ሊቆራኝ ይገባዋል፡፡ በንግግር ውስጥ ልዩ ልዩ የፊት ገጽታ መለዋወጦችና ድርጊቶች ይኖራሉ፡፡ ስለሆነም በንግግሩ ወቅት የሚፈጠረውን የአካል እንቅስቃሴ የሚያመላክቱ ድርጊቶች መጠቀም አለባቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች ልክ እንደድምጸቱ ሁሉ በመድረክ መግለጫ ሊጠቆሙ ይችላሉ፡፡

ምሳሌ፡- አሳላፊ፡- (ፈገግ ብሎ እጅ እንደመንሳት ይልና) ስምዎን ባለማወቄ ይቅርታ

ያርጉልኝ ጌታዬ---ለወደፊቱ አይደግመኝም፡፡

ከዚህ ውጪ ግን የተጋነነ ማብራሪያ ማስፈር  አላስፈላጊ ነው፡፡ ተውኔት በጥቂት ጊዜ ብዙ የሚባልበት ጥበብ ስለሆነ ባይገለጽ የማያጎድል ሀሳብ ካለ መቅረትና አስፈላጊው ብቻ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

ጸሐፌ ተውኔቱ ገጸባህሪያትን በሚቀርጽበት ጊዜ ለነሱ የሚሆን የአነጋገራቸውን ሁኔታና ተገቢ የሆነውን ድምጽ ፈልጎ ማግኘት በጣም አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፡፡ የያንዳንዱ ገጸባህሪ አነጋገርና የሚጠቀማቸው ቃላት ከማንነቱ ጋር የሚሄድና ከሌሎች ገጸባህሪያት የሚለየው መሆን አለበት፡፡ አንድ ገጸባህሪ ሁልጊዜ ሲናገር በአንድ ተለይቶ ሊታወቅ በሚችልበት የተለየ አይነት የአነጋገር ስልት መሆን አለበት፡፡ በተውኔቱ ውስጥ "ኸዚያ በኋላ" እያለ በተደጋጋሚ ሲናገር የቆየን ገጸባህሪ በቂ ምክንያት ሳይኖር "ከዚያ በኋላ" ላለማስባል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ተማሪዎች የዚህን ተውኔትን የተመለከተውን የትምህርታችንን ከማጠናቀቃችን በፊት የሚከተለው ባለአንድ ገቢር ተውኔት በምሳሌነት ቀርቦላችኋል፡፡ ተውኔቱን አንብባችሁ ከተማራችሁት ትምህርት ጋር ለማገናዘብ ሞክሩ፡፡